
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3566 | ቅዳሜ መጋቢት 19 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







## ታሪክ አሻጋሪው ስምምነት

4



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና የዓድዋ ድል መታሰቢያ በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል

## የተገልጋዮቹ ቅሬታና የተቋሙ ምላሽ

17



ፎቶ- ከገፀ ድር

የመንግስት ሰራተኞች በፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲገለገሉ

## ጥበብና ጥበበኞችን ያገናኙ ስፍራዎች

11



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከሰሞኑ በአራዳ ፖርክ የወጣቶች የኪነ-ጥበብ እና የስፖርት ፌስቲቫል ተካሂዷል

# የአዲስ አበባ መልክ በከተሜነት መነፅር

**“በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ ግዙፍ የልማት ስራዎች ከውበት ባለፈ የዜጎችን አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነ-ልቦናዊ ጤና ለመገንባት ታቅደው የሚተገበሩ ናቸው”**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከተማ፣ ከተሜነት፣ ክትመት እና የኮሪደር ልማት በሚል ርዕስ በሰጡት ማብራሪያ በመዲናዋ በተከናወኑ ልማቶች ዘርፈ ብዙ ስኬቶች እንደተመዘገቡ አመላክተዋል

# ለችግር የተጋለጡ ነዋሪዎችን

**“ከተረጂነት ወደ ምርታማነት በማሸጋገር ረገድ ተጨባጭ ለውጥ እየተመዘገበ ነው”**

**የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በደረጀ ታደሰ**

የዕለቱ የአየር ጠባይ ቀዝቃዛና ደመናማ የሚባል አይነት ነው፡፡ የአየር ሁኔታው ሳይበግራቸው በአዲስ አበባ ስታዲየም በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች፣ ሴቶችና እናቶች ተሰባስበዋል፡፡ ለእነዚህ ሠዎች የአየር ጠባይ መለዋወጥ በእንቅስቃሴያቸው ላይ ብዙም ተፅዕኖ እንደማያመጣ ገጽታቸው ይመሰክራል፡፡ ያለፉበት የሕይወት ጉዞ ለዚህ ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህ ለላቀ ፈተና እንዳይረቱ አድርጓቸዋል፡፡ የሥራ ሰዎች፣ ሠርቶና ጥሮ አዳሪዎች ናቸው፡፡ በሥራቸው ከእነሱ ባለፈ፣ ቤተሰባቸውን፣ ከተማቸውንና አገራቸውን ለመለወጥ ራሳቸውን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የስራ ዕድል ተጠቃሚዎች ከተረጂነት ወደ ምርታማነት በተሸጋገሩበት የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ መልዕክት አስተላልፈዋል

# ለምርጫው ስኬታማነት የምሁራን ሚና

**በስንታየሁ ምትኩ**

ዛሬ ዓለም የምትሽከረከርባቸው ዋነኛ የሐሳብ ምህዋሮች በማመንጨት ምሁራን ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በምጣኔ ሀብት፣ በሳይንስ፣ በዴሞክራሲ፣ በቴክኖሎጂና በሌሎች መስኮች ሐሳብ በማመንጨት አሻራቸውን አሳርፈዋል። አለማየሁ አረዳ (ዶ/ር) “ምሁሩ” በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገለጹት፤ ምሁራን በኢትዮጵያ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስክ ያሉ ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን በማመንጨትና ለህብረተሰቡ በማሰራጨት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ምሁራን በመደማመጥ፣ በመከባበር፣ በመደራደርና


ወደ ገጽ 6 ዞሯል






**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ




## የስራ ዕድል ፈጠራው እየተተገበረ ያለበት መንገድ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!

በማንኛውም በማደግ ላይ ያለ ሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ወጣቱ የሰው ኃይል የጀርባ አጥንት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ኃይል ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በንድፈ-ሐሳብ ካገኘው እውቀት ባለፈ፣ በሥራው ዓለም በተግባር የተፈተነ ክህሎት ሲታጠቅ ብቻ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ነው። ዛሬ ላይ በመርሃ ግብሩ የሚሳተፉ ወጣቶች፣ ነገ የኢኮኖሚው ሞተር ሆነው ብቅ እንዲሉ ከማድረጉም በላይ፣ የሥራ አጥነትን ችግር ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት በውጤት እየታጀበ መሆኑን እያስመሰከረ ይገኛል።

ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ወጣቶችን በገበያው ውስጥ ተፈላጊና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደረገ ነው። ብዙ ጊዜ አዳዲስ ተመራቂዎች ወደ ሥራው ዓለም ሲገቡ የሚያጋጥማቸው ዋነኛ ተግዳሮት "ልምድ የላችሁም" የሚለው ነው። ይህ ፕሮግራም ግን ወጣቶች ገና ከጅምሩ ከዘመናዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ከሥራ አካባቢ ጋር በቀጥታ እንዲተዋወቁ በማድረግ ይህንን ማነቆ ይሰብራል። ወጣቶቹ በተግባር የታገዘ ሥልጠና ሲያገኙ፣ በራስ የመተማመን ስሜታቸው ከመጨመሩም በላይ፣ በየትኛውም የሥራ ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል የሙያ ልምድ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ይህ ስልት ለወጣቶቹ ብቻ ሳይሆን ለቀጣሪ ድርጅቶችም ጭምር ትልቅ ዕድል ነው። ተለማማጅ ወጣቶችን የሚቀበሉ ተቋማት፣ ትኩስ ኃይልና አዳዲስ እይታዎችን ወደ ድርጅታቸው ያስገባሉ። በሥራ ላይ ሥልጠናው ወቅት ወጣቶች ለድርጅቱ ባህልና አሠራር ራሳቸውን እያላመዱ ስለሚሄዱ፣ በቋሚነት ሲቀጠሩ ድርጅቱ ለተጨማሪ ሥልጠና የሚያወጣውን ወጪና ጊዜ ይቆጥብለታል። ይህም የድርጅቶችን ምርታማነትና ውጤታማነት በቀጥታ የሚያሳድግ ሲሆን፣ በግልና በመንግሥት ዘርፎች መካከል ያለውን ትብብርም ይበልጥ ያጠናክረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለመርሃ ግብሩ ከፍተኛ በጀት በመመደብና በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን በማሳተፍ እያከናወነ ያለው ተግባር የሚበረታታ ነው። ትናንት በምግብ ዋስትና እና ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም 15 ሺህ 492 ተጠቃሚዎች ከተረጂነት ወደ ምርታማነት መሸጋገር ችለዋል። ባለፉት አምስት ዓመታት በሴፍትኔት ፕሮግራም ውስጥ ታቅፈው የነበሩ ከ695 ሺህ በላይ ነዋሪዎችን ወደ ምርታማነት በማሸጋገር ራሳቸውን እንዲችሉ መደረጉም የሚበረታታ ተግባር ነው።

በከተማዋ ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ከተጀመረበት 2014 ዓ.ም ጀምሮ ትናንት የተመረቁትን 8 ሺህ 852 ወጣቶች ጨምሮ 49 ሺህ የሚሆኑ ዜጎች በተፈጠረላቸው ትስስር ወደ ሥራ ባለቤትነት ተሸጋግረዋል። ታዲያ ፕሮግራሙ በበርካታ ወረዳዎች ተደራሽ መሆኑና የተለያዩ የሙያ ዘርፎችን ማካተቱ፣ የወጣቶችን ዝንባሌና የገበያውን ፍላጎት ያገናዘበ መሆኑን ያሳያል።

በጥቅሉ ወጣቶችን በዚህ መርሃ ግብር ማብቃት ማለት የአንድን ከተማ የወደፊት ዕጣ ፈንታ መወሰን ላይ አይተኬ ሚና መጫወት ማለት ነው። ወጣቱ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርለት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ ለተፈጠረው ዕድል ብቁና ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኝ ማስቻል ደግሞ የሁላችንም ኃላፊነት ነው። ቀጣሪ ድርጅቶችም ይህንን ሀገራዊ ጥሪ በመቀበል፣ ወጣቶችን በማቀፍና በማሰልጠን ረገድ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል። መንግሥት የጀመረውን ይህን ውጤታማ መርሃ ግብር በዘላቂነት ማጠናከር፣ የከተማዋን የሰው ኃይል ወደ ብልጽግና ማማ የሚያሸጋግር ኃይል እንዲሆን በትጋት መሥራት ይኖርበታል።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## መገልገል መብት እንጂ ውለታ አይደለም!

**በእቴጌ ከካራቆሬ**

በማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋም ውስጥ አገልግሎት ፍለጋ የምንመላለስ ዜጎች፣ የምናገኘው አገልግሎት የመብታችን ውጤት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎትን በፍጥነት ለማግኘት ወይም "ጉዳይ ለማስፈጸም" በሚል የሚሰጥ "የእጅ መንሻ" (ጉቦ) በአገልጋይና በተገልጋይ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ሰጪና ተቀባይነት ይቀይረዋል።

አንድ ተገልጋይ ወደ መሥሪያ ቤት ሲመጣ የሚያገኘው መስተንግዶ በሠራተኛው በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ "ችሮታ" አይደለም። ይልቁንም ተቋሙ የተቋቋመበት ዓላማና ሠራተኛው የሚከፈለው ደመወዝ ያንን አገልግሎት በታማኝነት እንዲሰጥ ስለሚያስገድደው ነው። ስለዚህ ያለ አድልዎ መስተናገድ፣ ስለ አሠራሩ ግልጽ መረጃ ማግኘትም ሆነ አገልግሎቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ መጠየቅ መብት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

ይህ ሲሆን፣ እንደ ተቋሙ ባሕሪ አንድ ባለጉዳይ የራሱንም ሆነ የሌላን ሰው መረጃ ሲጠይቅ በተቋሙ አሠራር መሠረት የሚጠየቀውን መስፈርት ለማሳያነት መታወቂያ፣ ሕጋዊ ውክልናም ሆነ ደብዳቤ መያዝ ካለበት አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል። አንዳንድ ተገልጋዮች እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ሲጠየቁ ወዳልተገባ እሳቤ የመሄድ አዝማሚያ ስለሚታይባቸው፣ ይህም ሊታረም ይገባል የሚል እምነት አለኝ።

ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች "ጥቂት ሳንቲም ብሰጥ ሥራዬ ይቀላጠፍልኛል" ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ለሥርዓት አልበኝነት በር ይከፍታል። ዛሬ ለአንድ ጉዳይ የሰጠነው ገንዘብ፣ ነገ ሌላው ዜጋ ያለ ገንዘብ እንዳይስተናገድ እንቅፋት ይሆናል። የእጅ መንሻ መስጠት የተቋሙን ወይም የድርጅቱን የአሠራር ጥራት ያበላሻል፤ ሐቀኛ ሠራተኞች ተስፋ እንዲቆርጡ ያደርጋል፤ ለአገር ኢኮኖሚና ለፍትሐዊ ተጠቃሚነትም እንቅፋት ይሆናል።

አገልግሎት ፈላጊ ወደ አንድ ተቋም ሲሄድ "እባክዎን ይርዱኝ" ከሚል ልመና ይልቅ "መብቴ ነውና አገልግሎቱን ላግኝ" የሚል የዜግነት መብትን መጠቀም ተገቢ ነው። አገልግሎት ለመስጠት ገንዘብ የሚጠይቅ ወይም ያለ በቂ ምክንያት የሚያንገላታ አካል ካጋጠመ፣ ለበላይ ኃላፊ ማሳወቅ ወይም ጥቆማ ማድረስ ይቻላል።

አሁን አሁን እየዘመኑ የመጡት የቴክኖሎጂ ውጤቶች (ዲጂታል አገልግሎቶች) ለብልሹ አሠራር ዋነኛው "መድኃኒት" ናቸው። የቴክኖሎጂ ሚና በዋናነት ሠራተኛውና ተገልጋዩ በቀጥታ እንዳይገናኙ በማድረግ ግልጽነትን መፍጠር በመሆኑ፣ ብሩህ ተስፋን እያየን ያለንበት ወቅት ላይ በመሆናችን የተሻለ ነገን እንድናልም የሚያደርጉን ናቸው ማለት ይቻላል።

አሁን እያየን ያለነው ዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂ ያለ እጅ ንክኪ የፈለግነውን ጉዳይ የምናስፈጽምበት ደረጃ ላይ እያንደረደረን ይገኛል። ይህ ሙሉ በሙሉ እውን ሲሆን የተገልጋይና የአገልጋይ ያልተገባ ግንኙነት ዘላቂ መፍትሔ ያገኛል፤ እንግልትም ይቀንሳል። ከፊታችን ያለውን ብሩህ ተስፋ ማጣጣም ደግሞ ከእኛ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው።

ያ እስኪሆን አገልግሎት ሰጪውና ተገልጋዩ እጅና ጓንት መሆን አለባቸው። አገልጋዩ በታማኝነት የመሥራት ግዴታ እንዳለበት ሁሉ፣ ተገልጋዩም መብቱን አስከብሮና ግዴታውን ተወጥቶ (ያለ እጅ መንሻ) መስተናገድ ይኖርበታል። ሙስና የሚቆመው አገልጋዩ "አልቀበልም" ሲል ብቻ ሳይሆን፣ ተገልጋዩም "አልሰጥም" ብሎ በኩራት መብቱን ሲጠይቅ ነው። ይህም "መብትህን እወቅ፤ በኩራት ተገልገል!" የሚለውን መርህ እንድንከተል ከማስቻሉም በላይ የዕድገት ጸር የሆነውን ሙስና ለማክሰም ትልቅ መሣሪያ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የአዲስ አበባ መልክ በከተሜነት መነፅር

**“በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ ግዙፍ የልማት ስራዎች ከውበት ባለፈ የዜጎችን አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነ-ልቦናዊ ጤና ለመገንባት ታቅደው የሚተገበሩ ናቸው”**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በመለሰ ተሰጋ**



ፎቶ- ከፋይል
በኮሪደር ልማቱ ውብ ገጽታን የተላበሰው የቦሌ አካባቢ ከፊል ገጽታ

አዲስም፣ አዲስ ነው፤ ያላረጀ ውበት፤ የዐይን ማደሪያ፤ አበባም አበባ፣ የቁንጅና ልኬት የንብ መነኸሪያ፡፡ በነዚህ ሁለት ጥምር ቃላት የምትጠራው አዲስ አበባ ደግሞ በብዙ መለኪያዎች በየዘመናቱ አዲስም፣ አበባም፣ ሆና እንደ ንጋት ጀምበር ደምቃ ትታያለች፡፡

በርግጥም አዲስ አበባ በዘመኗ አዲስም፣ አበባም እንደነበረች ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ዘመን እየገፋ አሳቢ እየጠፋ፣ አበባዋ እየጠወለገ፣ አዲስነቷ እያረጀ፣ እየደበዘዘ እና በስልጣኔ ምጥቀት እየተሻገረ መጥቶ ወደ ጎስቋላነት ተቀይሮ እንደነበርም የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡

በታሪክ መዝገብ ላይ በሰፈረው ገናና ክብሯ ግን አዲስ አበባ ዕድሜ፣ ወዝ፣ ለዛና ጣዕም ያላት ከተማ ናት፡፡ የሀገሪቱም ሆነ የአህጉረ አፍሪካ የስልጣኔ፣ የነፃነት፣ የአንድነት፣ የጀግንነት በር፣ የተስፋም መስኮት ናት፡፡

የከተሞች ከፍታና ዝቅታ ደግሞ እንደ ሀገር ያለው በረከትና መርገም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከተሞች የሀገራት ልብ ምት፣ የስልጣኔ መግቢያ በር፣ የምጣኔ ሀብት ርካብ፣ ቀን ነፍስና ስጋን ማስደሰቻ፣ ማታ ደግሞ ጨለማውን መርቻ የድል መቅረዝ ናቸው፡፡

የከተማ ኑሮ መሻሻል ምርታማነትን፣ ባህልን እና የሰው ልጆችን ደስታ ከፍ በማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት የከተማ ልማት ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ግሌዘር እ.ኤ.አ በጥር 31 ቀን 2012 ‘የከተሞች እውነት ወይም ድል’ (Triumph of the City) በተሰኘ ግሩም ጥናታዊ መፅሐፋቸው ላይ ገልጸውታል፡፡

በርካታ የዓለማችን ክፍል ቀን እንደነገሩ ውሎ አመሻሹን ሲያሸልብ ከተሞች ግን በተራራ ላይ እንደተለኮሰ ችቦ ብርሃንን እየፈነጠቁ በምድርቱ ላይ ያረበበውን ጨለማ እንደ አደይ አበባ በፈካ ውበታቸው እንዴት እንደሚገፍፉት ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ባማረ አገላለፅ፣ “ከተሞች የዓለማችን ሕይወት መቀጠል ምልክት፣ የልብ ትርታችን ምት ናቸው” በማለት በመፅሐፋቸው ከሽነውታል፡፡

ኒው ዮርክ ብዙ ጊዜ “ቀን ንቁ ማታ ደግሞ የማትተኛት ከተማ” እየተባለች ትጠራለች፡፡ ከተማዋ ቀን በተፈጥሮ ብርሃን ከፀሐይ ጋር ደምቃ ትውልና መሸት ሲል ደግሞ ከላይ በጨረቃና ከዋክብት፣ ከታች በዘመናዊ መብራቶች ትዋባለች፤ ትደምቃለች፡፡

አዲስ አበባም በዚህ ድል ምዕራፍ ላይ ትገኛለች፡፡ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሆስፒታሊቲ እና የቱሪዝም ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር ደመቀ ክብሩ እንደሚሉት በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለው ኮሪደር ልማት ከተማዋን ከቱሪስት መሸጋገሪያነት ወደ መዳረሻነት የቀረ፣ እንደ ኒው ዮርክ፣ ፓሪስና ለንደንን የመሳሰሉ ከተሞችን ፈለግ የተከተለ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ለአብነት የኮሪደር ልማቱ የከተማዋ የመንገድ መሰረተ ልማት እና የአረንጓዴ ሽፋን እጅግ ከፍ እንዲል አስችሏል። በከተማዋ ነባርና አዳዲስ ቱሪዝም መዳረሻዎች ዘመኑን በሚመጥን መልኩ ተገንብተዋል፡፡ ይህም ከቱሪዝም ኢኮኖሚው ባሻገር ለከተማዋ ነዋሪዎች አጠቃላይ ጤና ያለው ፋይዳ የላቀ መሆኑን ሁሉም የሚገነዘበው ጉዳይ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በኮሪደር ልማትና መሰል ተግባራት ከተማን ማዘመን ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ እና የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ አስመልክቶ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) በሰጡት ማብራሪያ፣ በየትኛውም ሁኔታ፣ ከፍታና ዝቅታም ውስጥ ቢሆኑ ከተሞች ለሰው ልጅ ሁለንተናዊ ስኬታማነት ያላቸው ሚና ላቅ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ስማርት መሆን ከከተማዋ ሁለንተናዊ ከፍታ ባሻገር እንደ ሀገር ትልቅ ኢኮኖሚያዊ እምርታ የሚያመጣ ነው ብለዋል፡፡

ከተሞች በዚህ ዘመን ላይ የስልጣኔ፣ የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሚባሉ ነገሮች ሁሉ ማዕከል ናቸው፡፡ በመሆኑም ከተማን ከስልጣኔ፣ ከዕድገት፣ ከልማት እና መሰል ዘመናዊ ነገሮች ልንለይ አንችልም ሲሉ አክለዋል፡፡

እንደ ይንገስ (ዶ/ር) በኮሪደር ልማቱም ሆነ በሌሎች ተግባራት ከተማዋ ስማርት ስትሆን የበለጠ ከተፈጥሮ ትታረቃለች፤ ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በሁሉም ዘርፍ በመጠቀም ከዘመኑ ትወዳጃለች፤ ይህ ሲሆን ደግሞ የአገልግሎት ተደራሽነት ይሰፋል። ቅልጥፍናውም ይጨምራል፡፡ ዜጎችም ህይወት በብዙ መልኩ ይሻሻላል፡፡

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት የከተማ ልማት ባለሙያና አማካሪ ኢንጂኒየር በሱፈቃድ ጌታቸው እንደሚሉት፣ የኮሪደር ልማቱ ካዛንቺስን፣ ዶሮ ማነቂያን፣ እሪ በከንቱን፣ ተረት ሰፈርን የመሳሰሉ የመዲናዋ አካባቢዎችን ውብ በማድረግ አዲስ አበባ የዘመናዊ ከተማ ገፅታን እንዲትላበስ አድርጓታል፡፡

እነዚህ ሀሴትን የሚያጎናፅፉ የልማት ስራዎች ከተማዋን ከዓለማችን ፅዱ፣ ውብና ተመራጭ ከተሞች ተርታ የሚያሰልፉ ናቸው፡፡ በተለይም ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ደስተኛ ሕይወትን እንዲመሩ የሚያስችሉ ስለመሆናቸውም ጠቁመዋል፡፡

የኮሪደር ልማቱ ሁሉን ያቀናጀ የከተማ ግንባታ (smart city) አካል በመሆኑ ለዘመናዊ ከተማ ግንባታ እንደ ሀገርም ሞዴል ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በከተማዋ እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት የሰውና የተሽከርካሪ መጓጓዣ መንገዶችን፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የመብራት፣ የስልክ እና ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታዎች፣ የመዝናኛና የማረፊያ ቦታዎች፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እና መሰል የማህበረሰቡን ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ መሆናቸው ደግሞ ስራውን የሚደነቅ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሄር ‘ትኩሳት’ ብሎ በሰየመው መጽሐፉ ጀርባ ፒያሳ ሂድ፤ ፒያሳ ወደ ሕይወት ትመልስሃለች እንዳለው፡፡ ደራሲ መሐመድ ሰልማን ደግሞ ‘ፒያሳ ማህሙድ ጋ ጠብቂኝ’ በተሰኘ ድንቅ ድርሰቱ የፒያሳን ውበት እንደ ጅረት እያፈሰሰ፣ እንደ ወንዝ እያገማሸረ አስኮምኩሞናል፡፡

“ፒያሳ አንድ ሺህ አንድ መቶ ካፌዎች ያሉባት ቅመም የሆነች ሰፈር ናት” እንዲል፡፡ በእርግጥ ይህ በዘመኑ እውነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ዶሮ ማነቂያ የመሳሰሉ አካባቢዎች እንደ ዘመኑ መዘመናቸው ቀርቶ ዘምመው አዲስ አበባም የትናንት ውበቷ በእርጅና ጉም ተሸፍኖ መልክና ስሟ አልገጥም ማለቱ ብዙዎቹን ማስቆጨቱ የአዘቦት ተረክ ሆኖ መቅረቱም የማይካድ ሀቅ ነበር፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የአዲስ አበባ ፀሐይ ደመናውን ገፍፋ የታሪካችን እምብርት በሆነው በዓድዋ ድል መታሰቢያ በኩል አድርጋ ዳግም በፒያሳ ላይ ወጥታለች፡፡ በዚህ ስፍራ የወጣችው ጸሐይም ከአብርሆት ቤተ መፅሐፍት እስከ እንጦጦ ፓርክ፣ ከወዳጅነት አደባባይ በየ አካባቢው እስከተገነቡት ውብ፣ ፅዳና ሰፋፊ መንገዶች እንዲሁም እንደ አዲስ በተወለዱት ቀበናን ወደ መሳሰሉ ወንዞች ድረስ የልማት ብርሃኗን እየፈነጠቀች ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ እየተከናወኑ ያሉ ግዙፍ የልማት ስራዎች ከከተማ ውበት ባለፈ የዜጎችን አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነ-ልቦናዊ ጤና ለመገንባት ታቅደው የሚተገበሩ መሆናቸውን ሰሞኑን ከቃና ቴሌቪዥን ጋር በከተማ፣ በከተሜነት፣ በክትመትና በኮሪደር ልማት ዙሪያ በነበራቸው ቆይታ የሰጡት ማብራሪያ አንዱ ምስክር ነው፡፡

ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ማዕከል ያደረገው ይህ የልማት እንቅስቃሴ፣ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲኖሯት በማድረግ ጤናማ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያለመ መሆኑንም ገልጸዋል።

ጤና ማለት የአካል ብቃት ብቻ ሳይሆን የአመጋገብና የዕለት ተዕለት የአኗኗር ዘይቤ ድምር ውጤት በመሆኑ፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችም ይህንን እሴት ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን አብራርተዋል። የአእምሮ ጤናንና የንባብ ባህልን ለማጎልበት የተገነቡት የአብርሆት ቤተ-መጻሕፍትና የሳይንስ ሙዚየም ለነገዋ ኢትዮጵያ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑንም መስክረዋል፡፡

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

# ታሪክ አሻጋሪው ስምምነት

- አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የዓድዋን ድል ታላላቅ ታሪኮች ለዓለም በማስተዋወቅ እና ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና እያበረከተ እንደሚገኝ ተመላክቷል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ከተሞች የሕዝብ መኖሪያ ብቻ አይደሉም፤ የሀገርን የሥልጣኔ ደረጃ የሚለኩ፣ የኢኮኖሚውን የልብ ትርታ የሚያሳዩና የዜጎችን የነገ ተስፋ የሚሰንቁ ሕያው ምስሎች እንጂ። አንድን ሀገር እንደ ሰው ብንመስለው፣ ከተሞች የዚያ አካል 'እጅና አእምሮ' ናቸው። በዕቅድና በጥበብ የሚመሩበት አዕምሮ፣ የልማትና የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸው ጠንካራ እጆችም ጭምር ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ ከተሞች የሀገር እጅና አዕምሮ እንዲሁም የሀገር መኳያ ናቸው።

ዛሬ ላይ በከተሞች የሚገነቡ ታላላቅ ሜጋ ፕሮጀክቶችና የውበት መገለጫዎች ደግሞ ተራ የግንባታ ውጤቶች ብቻ አይደሉም። እነዚህ ፕሮጀክቶች የከተማን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ የነዋሪዎችን ማኅበራዊ ትስስር የሚያጠናክሩ፣ ለቱሪዝም መስህብነት የሚመቹና ከተሞች 'የሀገር መኳያ' ሆነው እንዲወጡ የሚያስችሉ የለውጥ ሞተሮች ናቸው። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ደግሞ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ቀዳሚው ነው።




ፎቶ- በገነት ወንድሙ

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ እና የዓድዋ ድል መታሰቢያ ዋና ዳይሬክተር ዮሴፍ ቤኮ (ዶ/ር) ሁለቱ ተቋማት በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት በተፈራረሙበት ወቅት

> "አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና የዓድዋ ድል መታሰቢያ ጥምረት ከተሞች 'የሀገር እጅና አዕምሮ' ናቸው ለሚለው እሳቤ ተግባራዊ ማሳያ ነው፡፡ የዓድዋ ድል መታሰቢያ እንደ 'እጅ' የታሪኩን አሻራ ጨብጦ ሲይዝ፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ደግሞ እንደ 'አዕምሮ' ታሪኩን ተንትኖና አቀናጅቶ ለዓለም ያሰራጫል"

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ከተሞች 'የልማት እጅ' መሆናቸውን በተግባር ያሳየ ደማቅ አሻራ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ። የዓድዋ ድል መታሰቢያ የከተማዋን ውበትና ግርማ ሞገስ ከመጨመር ባለፈ፣ ለቱሪዝም፣ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለተለያዩ ማኅበራዊ መስተጋብሮች ሰፊ በር በመክፈት የከተማዋን ሁለንተናዊ ፋይዳ ከፍ አድርጎታል። እንደነዚህ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች በከተማ ውስጥ መገንባታቸው፣ ከተሞች የሀገር መለያና የሥልጣኔ መድረክ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሲሆን፤ ነዋሪዎችም በከተማቸው ታሪክና ዕድገት እንዲኮሩ፣ የነገዋን ዘመናዊት ኢትዮጵያን በልበ-ሙሉነት እንዲያልሙ ትልቅ ሥነ-ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ስንቅ ይሆንላቸዋል ማለት ይቻላል።

መገናኛ ብዙኃን ደግሞ የከተማ ፕሮጀክቶችን ታሪክና ፋይዳ ለሕዝብ ተደራሽ በማድረግ ረገድ እንደ መስታወት ሆነው ያገለግላሉ። እንደ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ያሉ ፕሮጀክቶችም ካላቸው ግዝፈት አንጻር፣ ሚዲያው የህንፃዎቹን ውበት ብቻ ሳይሆን በስተጀርባ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታዎች በዝርዝር በመተንተን ዜጎች በልማቱ ላይ ባለቤትነት እንዲሰማቸው ያደርጋል። ይህም በሕዝብና በመንግሥት መካከል ጠንካራ የመረጃ ድልድይ በመገንባት፣ ፕሮጀክቶቹ የሀገር ኩራትና የሥልጣኔ መገለጫ መሆናቸውን በሰፊው በማስተዋወቅ ረገድ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ።

የዓድዋ ድል ለጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፋና፣ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ የጽናት ማኅተም ነው። ሆኖም ይህ ግዙፍ ታሪክ ትርጉሙ ጎልቶ የሚወጣውና ለትውልድ የሚሻገረው በዘመኑ ቋንቋ ተቀርጾና ተሰንዶ ሲቀርብ ጭምር ነው። አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ይህንን ታሪካዊ ኃላፊነት ተረክቦ የጥቁር ሕዝቦች ድል የሆነውን የዓድዋን ገድል በተንቀሳቃሽ ምስልና በፊልም ለማሰናዳት ከሰሞኑ ስምምነት ተፈራርሟል።

ይህ ስምምነት የከተማዋን ታሪክ መዘክር ብቻ ሳይሆን፣ በየዕለቱ የሚታይና የሚሰማ የሥልጣኔ ትርክት ማዕከል ያደርጋታል። ሚዲያውና ሙዚየሙ የተፈራረሙት ይህ ውል፣ ሙዚየሙን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታይ የኪነ-ጥበብ ፈርጥ የማድረግ ታላቅ የከተማ ግንባታ ሥራ አካል ነው።

የጥቁር ሕዝቦች ድል የሆነው የዓድዋ ድል ታሪክ በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም በፊልም ተሰንዶ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር እንደሚሰራም የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ ገልጸዋል።

የመግባቢያ ስምምነቱን የፈረሙት የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ፣ ኤ ኤም ኤን የዓድዋን ድል ታላላቅ ታሪኮች አጉልቶ ከማውጣት፣ ለተቀረው ዓለም ከማስተዋወቅ እና ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ከማድረግ ረገድ በርካታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የመዲናዋ ፈርጥና የቱሪዝም መስህብ የሆነው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ግንባታ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እና ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ በኋላም የዓድዋን ታሪኮች በተለያዩ ቋንቋዎች ለሕዝቡ ተደራሽ በማድረግ እና የጋራ ታሪክን በማጽናት ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ መሆኑን ገልጸዋል የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን። አክለውም፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ የዓድዋ ድል ታሪክ በአግባቡ ተሰንዶ ለቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍበት ስፍራ መሆኑንም አስረድተዋል።

የዓድዋ ድል ታሪክ በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም በፊልም ተሰንዶ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ከማድረግ አንጻር የዓድዋ ድል መታሰቢያን ጨምሮ የከተማ አስተዳደሩ፣ ምሁራን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ሊሠሩ ይገባል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ኤ ኤም ኤንም ኃላፊነቱን እንደሚወጣ ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ዋና ዳይሬክተር ዮሴፍ ቤኮ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ አባቶቻችን ትልቅ ዋጋ ከፍለው የተከበረች ሀገር አውርሰውናል፤ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም ይህንን ታሪክ አጉልቶ ከማውጣት፣ ለተቀረው ዓለም ከማስተዋወቅና ለትውልድ እንዲተላለፍ ከማድረግ ረገድ የላቀ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ፓን አፍሪካኒዝም፣ ዓድዋና ሕዳሴ የማይለያዩ ጉዳዮች ናቸው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እነዚህን የወል ታሪኮች በማስተዋወቅ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ሲሉ ይገልጻሉ። ሁለቱ ተቋማት የበለጠ ተቀራርበው ለመሥራት የሚያስችላቸውን ፊርማ ማኖራቸውም ለከተማዋ ብሎም እንደ ሀገር ለተያዙ ትልሞች የሚጫወተው ሚና የጎላ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየሙ ጥምረት ከተሞች 'የሀገር እጅና አዕምሮ' ናቸው ለሚለው እሳቤ ተግባራዊ ማሳያ ነው። የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየሙ እንደ 'እጅ' የታሪኩን አሻራ ጨብጦ ሲይዝ፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ደግሞ እንደ 'አዕምሮ' ታሪኩን ተንትኖና አቀናጅቶ ለዓለም ያሰራጫል።

በፊልም የታገዘ ሰነድ ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ የማይደበዝዝ የታሪክ ቅርስ ከመሆኑም ባለፈ፣ አዲስ አበባን በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ካርታ ላይ የጥቁር ሕዝቦች የክብር መዳረሻ አድርጎ ይስላታል። የከተማ ፕሮጀክቶች ፋይዳቸው የሚጎላው እንዲህ ካሉ የሚዲያ ሥራዎች ጋር ሲጋቡ መሆኑን ስንመለከት፣ ይህ ስምምነት ከተማዋን 'ለመኳል' የተጀመረው ጉዞ አንድ እርምጃ ወደፊት መራመዱንና የታሪካችን ድምፅ በምስል ታጅቦ ዓለምን እንዲያነጋግር በር መከፈቱን ያረጋግጣል።

በእርግጥ ይህ በአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ እና በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም መካከል የተደረገው ስምምነት አዲስ ክስተት ሳይሆን፣ ተቋሙ ላለፉት ዓመታት ከተለያዩ ስትራቴጂካዊ አጋሮች ጋር ሲያከናውናቸው የቆያቸው ስኬታማ ትብብሮች ቀጣይ አካል ነው። አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ ቀደም ከከተማዋ ታላላቅ የልማት ተቋማት ጋር በመቀናጀት፣ የከተማዋን ሜጋ ፕሮጀክቶች ገጽታ ለነዋሪውና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማስተዋወቅ ረገድ ውጤታማ ተግባራትን አከናውኗል።

ለአብነት ያህል፣ ተቋሙ ከአዲስ አበባ ሜጋ ፕሮጀክቶች ቢሮ ጋር በመሆን እንደ መስቀል አደባባይ ያሉ ግዙፍ ግንባታዎችን ሂደት ከመጀመሪያው እስከ ፍጻሜው በመዘገብ፣ የፕሮጀክቶቹን ምህንድስናና ማኅበራዊ ፋይዳ ለሕዝብ ግልጽ አድርጓል። በተጨማሪም ከአዲስ አበባ ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመቀናጀት 'እንኳን ደህና መጡ' በሚሉና መሰል የቱሪስት መዳረሻዎችን በሚያስተዋውቁ ፕሮጀክቶች ላይ በጋራ በመሥራት፣ የከተማዋን የቱሪዝም ፍሰት ለማሳደግ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

እንደዚሁም ከጤና እና ከትምህርት ቢሮዎች ጋር የሚደረጉት ዘላቂ የሚዲያ ስምምነቶችም ተቋሙ የልማት አጋርነቱን በተግባር ያረጋገጠባቸው ማሳያዎች ናቸው። እነዚህ የተከማቹ ልምዶች አሁን ከዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ጋር ለተጀመረው የታሪክ ሰነድ ዝግጅት እንደ ትልቅ ግብዓት የሚያገለግሉ ሲሆን፣ የሚዲያ ተቋሙ ካለው ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አቅም ጋር ተዳምሮ የዓድዋን ታሪክ በላቀ ጥራትና ጥልቀት ለማቅረብ ዋስትና ይሆናሉ።

# ለችግር ... ከገጽ 1 የዞረ

ያበቁም ናቸው፡፡ በእነዚህ መካከል የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ መገኘታቸው ደግሞ፤ ለተሰብሳቢዎች የበለጠ መነቃቃትን የፈጠረ ሆኗል፡፡ ቀዝቃዛው እና ደመናማው የአየር ጠባይ በአዲስ አበባ ስታዲየም በነበረው ሁነት ተረትቷል። ተስፋ፣ ሙቀት፣ ኃይልና ብርታት ሰፍኗል።

የትላንትናዋ (የመጋቢት 18 ቀን 2018 ዓ.ም.) ማለዳ ልዩ መሆኗን ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ከተረጂነት ወደ አምራችነት መሸጋገራቸውን በማብሰር ነበር የገለጹት። በዕለቱ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ እና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ታቅፈው የቆዩና ያጠናቀቁ 15 ሺህ 492 ተጠቃሚዎች ተመርቀዋል። ከእነዚህ ውስጥ 8 ሺህ 852 ወጣቶች የብቃት የሥራ ልምምድ መርሃ ግብርን ያጠናቀቁ ናቸው፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከተረጂነት ወደ ምርታማነት የተሸጋገሩ ተመራቂዎች በከፊል

የተጠቃሚዎችን ምረቃ መርሃ ግብር መነሻ በማድረግ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በይፋዊ የፌስ ቡክ ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ "ከተማችን አዲስ አበባ ለችግር የተጋለጡ ነዋሪዎችን ከተረጂነት ወደ ምርታማነት በማሸጋገር ረገድ ተጨባጭ ለውጥ እያስመዘገበች ትገኛለች። ይህ ተግባር በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ ከተደረጉት አምስቱ የ'ዜሮ ግቦች' መካከል አንዱና ዋነኛው የሆነው 'ተረጂነትን እና ልመናን ዜሮ የማድረግ' ታላቅ ርዕይ በከተማችን ስኬታማ እየሆነ መምጣቱን ማሳያ ነው" ብለዋል፡፡

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ በበኩላቸው ቢሮው ድህነት ዕጣ ፈንታ አለመሆኑንና በአስተሳሰብ ለውጥ ማሸነፍ እንደሚቻል የግንዛቤና የመግባባት ሥራ በመሥራቱ ተጠቃሚዎች ለለውጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

አቶ ሚሊዮን አክለውም ተጠቃሚዎች ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት አስፈላጊው የስነ-ልቦና የሕይወት ክህሎትና የንግድ ሥራ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። ለዚህም እንደ መነሻ የሚሆን የገቢ ማስገኛ ሥራ ማስጀመሪያ ድጋፍ የተመቻቸላቸው ሲሆን ይህም ዜጎች በገበያው ውስጥ በራስ መተማመን እንዲንቀሳቀሱ አቅም ሆኗቸዋል።

በተጨማሪም ተጠቃሚዎች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ከመንግሥታዊ ተቋማት ባሻገር ከመንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከግል ዘርፉ ጋር የማቀናጀት ሥራ ተሠርቷል። ይህም ተጠቃሚዎች ሰፊ የገበያ ትስስርና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ሽግግሩን ይበልጥ እንዳፋጠነው አብራርተዋል።

የምግብ ዋስትና ፕሮግራም እና የብቃት የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ተግባራዊ መሆንና ዜጎችን መጥቀም ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ሲተገበር መቆየቱን በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ መርሃ ግብሩ በቆየባቸው ጊዜያት በትላንትናው ዕለት የተመረቁትን 8 ሺህ 852 ወጣቶች ጨምሮ 49 ሺህ የሚሆኑ ዜጎች ከተረጂነት እና ሥራ አጥነት ወጥተው በተፈጠረላቸው ትስስር የሥራ ላይ ልምምድ አጠናቀው ወደ ስራ ባለቤትነት እና አምራችነት ተሸጋግረዋል።

የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር፣ ለመዲናዋ ወጣቶች ሁነኛ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ሆኖ ስለማገልገሉ ከዚህ ቀደም የተከናወኑ የመርሃ ግብሩ የሁለት ዙር ፍሬያማ ውጤቶች ምስክር ናቸው፡፡ በሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር የታቀፉ ወጣቶች፡- ከሥራ አጥነት ተላቅቀው፣ የነበረባቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ ጫና አስወግደው፣ ከጥገኛነት ራስን ወደ መቻል ተሸጋግረው፣ ተስፋ መቁረጥን በሥራ ስለት ቆርጠው፣ ዛሬን በጥረት ነገን በተሻለ ርዕይ ቀርፀው ... ጉዞ ወደፊት የሚል ወኔን የተላበሱ የተግባር ሠዎች ወደ መሆን መቀየራቸውን ከአንደበታቸው ሰምተናል፡፡ በሥራ ቦታቸው ተገኝተን ተመልክተናል፡፡ በአሠሪ ድርጅቶች ምስክርነትም አረጋግጠናል፡፡

ነዋሪነታቸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሆኑት ወጣት ገነት ረጋሳ እና ወጣት ቤተልሔም ኪዳነማርያም፣ በሦስተኛው ዙር ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ታቅፈው በትላንትው ዕለት በይፋ ከተመረቁት ወጣቶች መካከል ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ወጣቶች በክፍለ ከተማው በሚገኝ ዮኬት ማኑፋክቸሪንግ ድርጅት ውስጥ በመግባት የሥራ ላይ ልምምድ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በልብስ ስፌት ሥራ ላይ በተሠማራው ድርጅት ውስጥም ተገቢ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድና መልካም የሥራ ስነ ምግባር በመላበስ በድርጅቱ ቋሚ ሠራተኛ ለመሆን በቅተዋል፡፡

እነዚህ ሁለት ወጣቶች እንደ ከተማ አስተዳደር ተግባራዊ በሆነው የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር በእጅጉ መጠቀማቸውን በቅርቡ ከጋዜጣችን ጋር አድርገውት በነበረው ቆይታ መስክረዋል። እንደ ወጣት ገነት ረጋሳ ገለፃ፤ በመርሃ ግብሩ ከመታቀፏ በፊት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈትና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት የሚያስችል ውጤት ባለማምጣቷ ምክንያት ተስፋ ቆርጣ በቤት ውስጥ ለመቀመጥ ተገድዳ ነበር። ከትምህርት ውጪ ምንም ዓይነት ለሥራ የሚያበቃ ሙያም ሆነ ልምድ ስለሌላት ያለሥራ ለወራት እንድትቆይ አድርጓት ነበር፡፡ ስለ መርሃ ግብሩ ያገኘችው መረጃ ያሳለፈችውን ያለሥራ በቤት የመቀመጥ አስቸጋሪ ጊዜ እንዲያከትም ምክንያት ሆኗታል፡፡

በራሷ ምርጫ ወደ አልባሳት ኢንዱስትሪ የተቀላቀለችው ወጣት ገነት፣ በመርሃ ግብሩ አማካኝነት የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስዳለች፡፡ በሦስት ወራት የሥራ ላይ ልምምድ ቆይታዋም ጨርቅ መቁረጥ፣ ኦቨርሉክ ማድረግ እና መስፋት የመሳሰሉ መሠረታዊ ሙያዎችን በሚገባ ተክናለች። "የሥራ ላይ ልምምድ እንዳጠናቀቅሁ ድርጅቱ በቋሚነት ቀጠረኝ፤ አሁን በወር 5 ሺህ 500 ብር ደመወዝ ይከፈለኛል" በማለትም በአጭር ጊዜ ውስጥ የሙያ እና የስራ ባለቤት እንድትሆን ስላደረጋት መርሃ ግብር በኩራት ትናገራለች። ገነት አክላም አብዛኞቹ ወጣቶች በመንግስት ተቋማት መቀጠርን ብቻ እንደሚጠብቁና ይህ ሳይሳካ ሲቀር ተስፋ እንደሚቆርጡ ጠቁማ፣ በየአካባቢው ያሉ ዕድሎችን መጠቀም እንደሚገባ ትመክራለች። በቀጣይም ከምታገኘው ገቢ በመቆጠብ የግል ሥራዋን የመጀመር ትልቅ ህልም እንዳላት ገልፃለች።

የ10ኛ ክፍል ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ለስድስት ወራት ያለ ሥራ በቤት ውስጥ መቀመጧ ለከፍተኛ ድብርትና ጭንቀት ዳርጓት እንደነበር የምታስታውሰው ወጣት ቤተልሔም ኪዳነማርያም፤ በወጣት ገነት ሃሳብ ትስማማለች፡፡ "እነዚያ ጊዜያት በጣም ረጅምና አሰልቺ ነበሩ" የምትለው ቤተልሔም፣ በሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብሩ አማካኝነት ወደምትወደው የአልባሳት ሙያ በመቀላቀሏ፣ ዕድሉ ከህልሟ ጋር ለመገናኘት እንደድልድይ እንደጠቀማት ትናገራለች። አሁን ላይ ስፌት የመስፋትና ፓተርን የማውጣት ሙያን ተክናለች፡፡ ከቤተሰብ ጥገኝነት ወጥታለች፡፡ ሙያዊ ክህሎቷን፣ ዕውቀቷንና የሥራ ሥነ ምግባሯን ከማሻሻሏ በተጨማሪ፣ ከድርጅቱ ባለቤቶች ያገኘችው ልምድ ለቀጣይ ህይወቷ ትልቅ መሠረት ሆኗታል።

የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር፣ ሥራ አጥ ወጣቶችን ከተረጂነት ወደ አምራችነት በዘላቂነት እንዲሸጋገሩ ትልቅ አቅም ከመፍጠሩ ባሻገር፤ ለአምራች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሙያ የበቃ የሠው ኃይል እንዲያገኙ ዕድል ማመቻቸቱን የድርጅት ባለቤቶች ይናገራሉ፡፡ ወጣት ገነት ረጋሳ እና ወጣት ቤተልሔም ኪዳነማርያምን ጨምሮ 30 ወጣቶች ተቀብሎ የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ያስቻለው የዮኬት ማኑፋክቸሪንግ ድርጅት ከተጠቃሚዎቹ አንዱ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የድርጅቱ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ቤዛዊት ነጌሶ እንዳስረዱት፣ ከሥራና ክህሎት ቢሮ የተቀበሏቸውን ወጣቶች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ልምምድ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል አድርገውላቸዋል፡፡ ወደ ድርጅቱ የገቡት ወጣቶች ሙሉ ለሙሉ ልምምዱን በሚገባ በማጠናቀቃቸው፣ ሙያዊ ክህሎትንና የሥራ ሥነ ምግባርን በመላበሳቸው ሁሉም በድርጅቱ በቋሚነት መቀጠር ችለዋል፡፡ በዚህም ከድርጅቱ ጋር በሥራም፣ በሥራ ባህልም የተግባቡ ብቁ ሙያተኞችን አግኝተዋል፡፡

በአስር ሺዎች ለሚቆጠሩ ወጣቶች ቋሚ የሥራ መፍጠሪያ የሆነው የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር፣ ለወጣቶች ቋሚና ዘላቂ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና ስለመጫወቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብህዲን ሱልጣን ያረጋግጣሉ፡፡ ለዚህ መርሃ ግብር ስኬታማነት የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ አዳነች አበቤ እና በየደረጃው ያሉ መአራሮች እንዲሁም የዓለም ባንክ ያደረገው የበጀት ድጋፍ ሚና የላቀ ሚና እንዳለው በመጥቀስ አድንቀዋል፡፡

አያይዘው እንዳብራሩት፤ የዓለም ባንክ ፕሮጀክት የመጨረሻ ምዕራፍ በሆነው የሦስተኛው ዙር የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር የታቀፉና በትላንትናው ዕለት በይፋ የተመረቁ ወጣቶች፣ የስድስት ወራት ቆይታቸውን ያጠናቀቁ እና በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ቋሚ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ናቸው፡፡

መንግሥት የመርሃ ግብሩን ውጤታማነት በማየት፣ በመንግስት ሙሉ ወጪ የሚከናወን 4ኛ ዙር የፓይለት ፕሮግራም በ115 ሚሊዮን ብር በጀት፣ በተመረጡ 20 ወረዳዎች፣ 3 ሺህ ወጣቶችን በመያዝ መጀመሩን የገለጹት አቶ ሰብህዲን፤ ይህ ተግባር እንደ ከተማ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሥራ አጥነት ቁጥርን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ መሆኑ ታምኖበታል ብለዋል።

በመጨረሻም፤ ተጠቃሚዎችን ከተረጂነት ወደ ምርታማነት የማሸጋገር ይፋዊ የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፈዋል፤ "ውድ ተመራቂዎች፤ ከተማችን እንደ እናንተ ዓይነት ትጉ፣ ያገኙትን ዕድል አሟጥጠው በመጠቀም ሕይወታቸውን በዘላቂነት የሚለውጡ እና ለሌላውም አርአያ የሚሆኑ ብርቱ ወጣቶች ያስፈልጓታል። በቀጣይም ከራሳችሁ አልፋችሁ ለሌሎች የሥራ ዕድል የምትፈጥሩ እና በሰነቃችሁት ርዕይ፣ ባካበታችሁት ልምድ የድርጅት ባለቤቶች ጭምር እንደምትሆኑ የእስካሁኑ ትጋታችሁ ትልቅ ማሳያ ነው፣ በርቱ!"

## ለምርጫው ... ከገጽ 1 የዞረ

በመተጋገዝ የጋራ ሀገራዊ ተልእኮ መቅረፅ፣ ህብረተሰቡ የራሱን ዕድል በራሱ ተሳትፎ እንዲወስን በመፍትሔ ሐሳቦች በማስታጠቅ መምራት ይኖርባቸዋል፡፡

ከዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫዎች መካከል ምርጫ አንዱ ነው፡፡ ምርጫ ዜጎች ይመራኛል፣ ሀገርን ወደ ተሻለ የዕድገት ደረጃ ያሸጋግራል ብለው የሚያምኑበትን አካል የሚመርጡበትና ኃላፊነት የሚሰጡበት ሥርዓት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ 7ኛውን ጠቅላላ ምርጫ ለማካሄድ ሽር ጉድ እያለች ትገኛለች፡፡ መራጮች የመራጭነት ካርድ እያወጡ ይገኛሉ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በተለያዩ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የምርጫ ክርክሮችን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ምርጫ ቦርድ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ መገናኛ ብዙኃን እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝነት አለው፡፡ ምሁራንም እንደ አንድ የማህበረሰብ ክፍል በምርጫው ውጤታማነት ላይ የሚጫወቱት ሚና ይኖራል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁር መኮንን አለሸኝ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ የዴሞክራሲ አንዱ ምሰሶ እንደመሆኑ ውጤታማና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ ማለት ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር መተግበር ማለት ነው፡፡ ጠብን፣ ጥላቻንና ደም መፋሰስን በማስቀረት የሥልጣን ሽግግር በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ የሚያስችል መሣሪያ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ነጻ፣ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሐዊና ተአማኒነት ያለው ሆኖ እንዲጠናቀቅ ምሁራን አይተኬ ሚና እንዳላቸው ዶ/ር መኮንን ያነሳሉ፡፡ በእርግጥ ምሁራኑ በየሀገራቱ እንዳለው የፖለቲካ ነጻነትና የዴሞክራሲ ዕድገት ደረጃ፣ የፖለቲካ መድረኩ መስፋትና መጥበብ ሚናቸው የሚወሰን ቢሆንም፤ በየትኛውም ሀገር በሀገር ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም ግንባታ ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡

ምርጫ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭ ህዝብ መሆኑ የሚረጋገጥበት ነው፡፡ 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ተአማኒነት ያለው እንዲሆን ምሁራን በቅድመ-ምርጫ፣ በምርጫና በድኅረ-ምርጫ ወቅት ወሳኝ ሚናዎችን መጫወት እንደሚችሉና እንደሚጠበቅባቸው መኮንን(ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡ በቅድመ ምርጫ ወቅት ዜጎች መምረጥና መመረጥ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መወሰን እንዲችሉና ሰላማዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለመራጮች የዜግነት ትምህርት በመስጠት ይሳተፋሉ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ፕሮግራሞችና የፖሊሲ ሐሳቦችን በጥልቀት በመተንተንና ለህዝቡ በማሳወቅ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲዎችና በጥናትና ምርምር ተቋማት የሚሰሩ ምሁራን በማስረጃ ላይ በመንተራስ የህዝብ ውይይትን በማበረታታት፣ የፖሊሲ ሪፖርቶችና ምርጫው በሰላምና ደህንነት እንዲሁም በኢኮኖሚ ረገድ


ፎቶ- ከፋይል
በጅማ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ዜጋ እና ስነ-ምግባር መምህርና ተመራማሪ ታሪኩ ተስፋዬ



ፎቶ- ከፋይል
ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የምሁራን ድርሻ ከፍተኛ ነው

የሚኖረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ጥናቶችን በማካሄድና ውጤቶችን በማቅረብ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በጅማ ዩኒቨርሲቲ በስነ-ዜጋ እና ስነ-ምግባር ጥናት ትምህርት ክፍል ውስጥ መምህርና ተመራማሪ ታሪኩ ተስፋዬ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ ምሁራን በማህበረሰብ ውስጥ ለሀገር የሚጠቅሙ አዳዲስ ሐሳቦችንና ዕውቀቶችን የማፍለቅና የማመንጨት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የምርጫው ሂደት ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ምሁራን በተለያዩ ፖለቲካዊ ጉዳዮች፣ በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫና በድኅረ ምርጫ ወቅት መከናወን ያለባቸው ሥራዎችን በተመለከተ በመረጃና በማስረጃ የተመሰረተ፣ ሳይንሳዊ አስተያየትና ትንታኔ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ምሁራን በምርጫው ሂደት የሚሳተፉ አካላት እውነታን በመያዝ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው የማስተማር ኃላፊነት እንዳለባቸው መኮንን (ዶ/ር) ያስረዳሉ። የምርጫውን ሂደት ፍትሐዊነት መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምርጫው ምን ያህል ፍትሐዊ እንደሆነ፣ ፍትሐዊ እንዲሆን ምን መሰራት እንዳለበት፣ ከማን ምን እንደሚጠበቅ በማስገንዘብ ረገድ ድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምርጫ ተቋማት ሙያዊ ምክር በመስጠት መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ተቋማቱ የሚመሩበት ደንብና አሰራር ያላቸው ቢሆንም የህዝብን ጥቅምና ፍላጎት ማዕከል አድርገው እንዲንቀሳቀሱ ተገቢውን ምክር በመስጠት ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ምሁራን በቅድመ ምርጫ ወቅት የምርጫ ተቋማት (ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት) ምርጫውን ለማካሄድ ያላቸውን ዝግጅት መተንተን፣ ክፍተቶች ካሉም እንዲስተካከሉ በመጠቆም ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ከምርጫው ጋር በተያያዘ ሊኖሩ የሚችሉ ብዥታዎችን፣ ወደ ግጭት ሊወስዱ የሚችሉ ነገሮችን

**ምሁራን ግጭትን የሚያስቀሩ፣ የሰላም ባህልና የኅብረተሰቡን አንድነት የሚያጠናክሩ ሀሳቦችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል**

ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጥናት ሕዝቡ በሰከነ መንገድ በምርጫው እንዲሳተፍ በማድረግ ረገድም ያላቸው አበርክቶ ቀላል እንዳልሆነ የስነ ዜጋ እና ስነ-ምግባር መምህሩ ታሪኩ ያስረዳሉ፡፡

ምሁራን ዜጎች የዜግነት መብትና ግዴታቸውን እንዲያውቁ የማስተማር ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከመብትና ግዴታ ጋር የተያያዙ እንደ መቻቻል፣ አብሮነት፣ መከባበርና ልዩነትን ማክበር ባሉ የዴሞክራሲ እሴቶች ዙሪያ ዜጎችን በማሳወቅ ረገድ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚኖርባቸውም ያክላሉ፡፡

በምርጫው ወቅት ደግሞ ምሁራን ገለልተኛ ታዛቢ በመሆን መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ለታዛቢነት ባይወከሉ እንኳን በራሳቸው እንደ ነጻና ገለልተኛ ታዛቢ ሆነው የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን፣ የምርጫውን ፍትሐዊነትና የሚፈጠሩ ችግሮች የሚፈቱበትን መንገድ ላይ መስራት እንደሚችሉ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

ሌላው በምርጫው ወቅት ሊያጋጥም የሚችለውን ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግርን በመከላከል ረገድ ምሁራን ሚና አላቸው፡፡ በመገናኛ ብዙኃን በተለይ በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ ሀሰተኛ መረጃዎችንና የጥላቻ ንግግሮችን በማጥራት፣ በመቃወምና በማጋለጥ ኃላፊነት የተሞላበት የፖለቲካ ውይይት እንዲፈጠር የድርሻቸውን መወጣት እንደሚችሉ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

ምሁራን ሰላማዊ የፖለቲካ ተሳትፎን ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እርስ በእርሳቸው፣ ከገዥው ፓርቲ ጋር ሲወያዩ፣ በመገናኛ ብዙኃን ሲቀርቡ፣ የምርጫ ዘመቻ ሲያካሂዱ ሰላማዊ ፖለቲካን በሚያበረታታ መልኩ መሆን አለበት፡፡ የፖለቲካ ልዩነትን ማቻቻልና መቀበልን ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ መራጩ ህዝብ እንዲላመድ በማድረግ ረገድ ደግሞ ምሁራን ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

የስነ- ዜጋና የስነ- ምግባር መምህሩ ታሪኩም ይህንን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ምሁራን ኅብረተሰቡ በሰላማዊ ውይይት እንዲሳተፍ፣ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መርሆችንና እሴቶችን እንዲገነዘብና እንዲተገብር፣ የህግ የበላይነት እንዲከበር በማሳወቅ በዴሞክራሲ ግንባታ ውስጥ ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡ በምርጫ ሂደቶች ውስጥ የፖለቲካ ውጥረቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ምሁራን ግጭትን የሚያስቀር፣ የሰላም ባህልና የኅብረተሰቡን አንድነትን የሚያጠናክሩ ሀሳቦችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ህግን ለማክበር፣ የዴሞክራሲ መርሆችን ለመጠበቅና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን ለማበረታታት የሚያግዙ ሐሳቦችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ምርጫው ፍትሐዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ነጻ እንዲሆን ያግዛል፡፡

በድኅረ-ምርጫ ወቅት ምሁራን የምርጫውን ውጤት በማስረጃ ላይ በመተንተን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በምርጫው በትክክል የመራጩ ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር? የምርጫ ሂደቱ ምን ጥንካሬና ድክመት ነበረው? ለወደፊቱ የሚጠቅሙ የተገኙ ትምህርቶችን በተመለከተ በሚገባ በመተንተን ለሕዝብና ለፖሊሲ አውጪዎች ምክረ ሐሳብ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

የስነ- ዜጋ እና ስነ- ምግባር መምህሩ ታሪኩ እንደሚናገሩት፣ በድኅረ ምርጫ ወቅት ምሁራን የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው፣ ሕዝቡ የምርጫ ውጤትን በሰላማዊ መንገድ እንዲቀበል የማስገንዘብ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሀገራቸው ጉዳይ የሚመለከታቸውና በምርጫው ሂደትም መከናወን ቢኖርበት ብለው የሚያምኑት የራሳቸው የሆነ ጥቅምና ፍላጎትም ይኖራቸዋል፡፡ ነገር ግን ይላሉ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር)፣ በምርጫው የራሳቸውን ሳይሆን ሀገራዊ ፍላጎትና አጀንዳን ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ምሁራን ያለ ወገንተኝነት፣ በገለልተኝነትና በኃላፊነት ሀሳባቸውን ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው የሚያነሱት የስነ ዜጋ እና ስነ- ምግባር መምህሩ ታሪኩ፣ ይህ የእውቀት ነጻነታቸው የተጠበቀ እንዲሆንና ኅብረተሰቡም ሐሳባቸውን እንዲገዛና ያላቸው ተአማኒ ወይም አምስት ሊሆን ይችላል፤ ድጋፍ

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የምርጫ ምንነት፣ መርሆች እና ዓይነቶች

## ክፍል ሦስት

ናደው ወርቁ (ዐቃቤ ህግ)

ውድ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው ዕትማችን በዋና ርዕሰ ጉዳይ የመራጮች ምዝገባ፣ የምዝገባ ጊዜ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ አስነብበናችኋል። ክፍል ሦስትን ደግሞ እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል። መልካም ንባብ!



### በምርጫ ወቅት የተከለከሉ ተግባራት

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 156 መሰረት በኢፌደሪ የወንጀል ህግ ምርጫን በሚመለከት የተደነገጉ የወንጀል ድንጋጌዎችን እና በአዋጁ የተከለከሉ ተግባራትን መፈጸም በወንጀል ያስቀጣል። እነዚህ የተከለከሉ ተግባራት ምን ምን ናቸው የሚለውን ቀጥለን እንመለከታልን።

### በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተከለከሉ ተግባራት እና ቅጣታቸው

በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 157 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በምርጫ ሂደት የሚከተሉትን ማድረግ በወንጀል ያስቀጣል፡፡

1. ከቦርዱ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ማተም፣ ማባዛት፣ መፈብረክ፣ ይዞ መገኘት ወይም ማደል በእስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፡፡

2. በድምጽ መስጫው ዕለት በድምጽ መስጫ ጣቢያ አካባቢ ድምጽ ከመስጠት ወይም የተሰጠን ህጋዊ ተግባር ከማከናወን ውጭ ሌላ ማንኛውንም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ መሳተፍ ወይም ባልተገባ ወይም በተከለከለ ጊዜ የምርጫን ውጤት ማተም ወይም ማባዛት ከ80 ሺህ ብር እስከ 100 ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡

3. የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ከ30 ሺህ እስከ 50 ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማያንስ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡

- በቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነት ላይ ጣልቃ ለመግባት መሞከር፣ መደለያ ወይም የተስፋ ቃል መስጠት ለመስጠት መሞከር፤
- ምርጫን ለማወክ ወይም እንዳይካሄድ ለማድረግ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም ውጤት ላይ ጫና ለመፍጠር በማሰብ ጥላቻን ወይም ፍርሃትን የሚቀሰቅስ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም በምርጫው ውጤት ላይ ጫና የሚፈጥር የሐሰት መረጃ አሳትሞ ማሰራጨት ወይም ለማሰራጨት ሙከራ ማድረግ፤
- የምርጫ ሚስጥራዊነትን መጣስ፤
- ከድምጽ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን መተላለፍ፤
- የቦርዱን ወይም የምርጫ አስፈጻሚዎችን እንቅስቃሴ ማወክ፤
- የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወይም የምርጫ ውጤት አገላለጽ፣ የመራጮች ወይም የፓርቲዎችን መብት አስመልክቶ የተጣሉ ክልከላዎችን መጣስ፡፡

4. የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም በ50 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡

- ሆን ብሎ የቦርዱ፣ የምርጫ ዋና አስፈጻሚው፣ የቦርዱ ሰራተኛ ስልጣኑን ወይም ተግባሩንና ኃላፊነቱን በሚያከናውንበት ወቅት እንቅፋት መሆን ወይም ማደናቀፍ፤
- የቦርዱን የስብሰባ ሂደት ሆን ብሎ ማቋረጥ ወይም በእነዚሁ ቦታዎች በማንኛውም ሁኔታ ያልተገባ ተግባር መፈጸም፤
- ሆን ብሎ በቦርዱ የስራ ቦታ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ ለማሳደር ሲባል ማንኛውንም የሀይል ተግባር መፈጸም፡፡

5. የምርጫ ማስታወቂያን ማጥፋት፡- ምርጫ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ውጤት እስከሚገለጽበት ቀን ድረስ የማንኛውንም እጩ ተወዳዳሪ ፖስተርን ወይም የምርጫ ማስታወቂያ ማበላሸት፣ ማስወገድ፣ ወይም መቅደድ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፡፡

6. ዓላማን በህገ ወጥ መንገድ ማስፋፋት፡- የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማ በኃይል ወይም በማስፈራራት ለማስረጽ ማንኛውንም ሰው ወይም ቡድን ማደራጀት ወይም ማሰልጠን ወይም ሰዎችን በግድ መመልመል እንዲሁም ይሄንን ተግባር ሲፈጸም መርዳት ወይም መተባበር በህግ ያስቀጣል፡፡

### በኢፌደሪ የወንጀል ህግ ምርጫን የተመለከቱ ድንጋጌዎች

በኢፌደሪ የወንጀል ሕግ በሕዝባዊ ምርጫዎችና በድምጽ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ከአንቀጽ 466 እስከ 476 ድረስ ተደንግጎ እናገኘዋለን። በዚህ መሰረት የሚከተሉት ድርጊቶች ወንጀል ናቸው፡፡

### 1. ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሂደትን ማወክና ማሰናከል (አንቀጽ 466)፤

በሕግ የተፈቀደን ከምርጫ ጋር የተገናኘ ሕዝባዊ ስብሰባን ወይም በሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ቁጥጥር በአግባቡ የሚደረግ የድምጽ አሰጣጥን ወይም ምርጫን አግባብ በሌለው በማንኛውም መንገድ ማወክ፣ መከልከል፣ ማደናቀፍ ወይም ማቋረጥ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል። በተጨማሪም በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የኃይል ድርጊት ተፈጽሞ ከሆነ ወይም የአምባጓሮ ወይም የሁከት ጠባይ ያለው ረብሻ ተነስቶ እንደሆነ አግባብ ያላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

### 2. የምርጫ ድምጽ የመስጠትን ወይም የመመረጥን መብት መንካት (አንቀጽ 467)፤

በዛቻ፣ በማስገደድ፣ በስልጣን ያለአግባብ በመጠቀም ወይም በኃይል ድርጊት፣ በማጭበርበር በተለይም ስምን በመለወጥ፣ ማስታወቂያን ወይም መጥሪያን በመደበቅ ወይም በማስቀረት ወይም በሌላ በማንኛውም ዘዴ፡-

- ሌላ ሰው በመምረጥ ወይም በመመረጥ መብቱ እንዳይጠቀምበት መከልከል፤
- ሌላ ሰው መብቱን በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ይህንኑ መብቱን ሳይጠቀምበት እንዲቀር ግዴታ እንዲገባ ማድረግ ወይም ማግባባት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፡፡
- በተጨማሪም ማንም ሰው እንደፍላጎቱ ለመጠቀም በተሰጠው መብት መሰረት የመምረጥ መብቱን በአንድ በተወሰነ መንገድ በተጠቀመበት ወይም ሳይጠቀምበት በቀረው ሰው ላይ በደል ወይም ጉዳት ማድረስ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል፡፡

### 3. በምርጫ ሂደት መደለያ መስጠት (አንቀጽ 468)፤

አንድ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለውን ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት ጥቅም መስጠት ወይም ለመስጠት ቃል መግባት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በመቀጮ ያስቀጣል፡፡

በተመሳሳይ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው አንድ ሰው በዚህ መብቱ እንዲጠቀምበት ወይም በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ሳይጠቀምበት እንዲቀር ገንዘብ ወይም ማንኛውንም ሌላ ዓይነት ጥቅም የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል፡፡

አንባቢዎቻችን ክፍል አራትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን፡፡

# የ"ባለጉዳይ" ቀን ለባለጉዳዩ እንዴት እየዋለ ነው?

**በሄለን ጥላሁን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትኩረት ሰጥቶ እየሠራባቸው ካሉ ተግባራት መካከል አንዱ አገልግሎት አሰጣጥ ነው። ለዚህ ደግሞ በየደረጃው ያለው አመራር ሚና ትልቅ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ረቡዕና አርብ የባለጉዳይ ቀን ተብሎ ለአገልግሎት የሚመጡትን እንዲያስተናግድ መደረግ ከተጀመረ ዋል አደር ብሏል፡፡ የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል ከዚህ አንጻር ያለው አሁናዊ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ቅኝት አድርጓል፡፡

ወይዘሮ ፅጌ መርሻ ይባላሉ፤ በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 7 ነዋሪ ናቸው፡፡ አዲስ አበባ ከተማ መኖር ከጀመሩ ከ45 ዓመት በላይ አስቆጥረዋል፡፡ በእድሜ አዛውንት የሚባሉ ናቸው፡፡ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸው በመሆናቸውና በቤት እጦት ምክንያት ኑሯቸውን ለመግፋት ቢያዳግታቸው በአካባቢያቸው ወደሚገኘው ወረዳ በማቅናት የቤት ጥያቄያቸውን በ2014 ዓ.ም አስገቡ፡፡ በዚህ ጊዜ 'ጥያቄዎት ምን ነበር?' ብሎ የሚያነጋግራቸው የመንግስት አካል አላጡም፡፡ የአራዳ ክፍለ ከተማ ቤቶች ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንዲሁም ዋና ስራ አስፈፃሚ የመጣሁበትን ጉዳይ ጠይቀውኛል፡፡" በማለት ባለጉዳይ ሆነው የሄዱበትን ምክንያትና ከሚመለከተው አመራር የተደረገላቸውን አቀባበል አስረድተዋል፡፡

"ክፍለ ከተማው ችግሬን በመስማት እኔ እዛው ባለሁበት የሚመለከተውን የወረዳ አመራር ደውሎ አጣርቷል፡፡ ቤት እንደሌለኝ እና እንደተቸገርኩ ቀጠና ላይ የሚገኙ የኅብረተሰብ ተወካዮች የጻፉልኝ ደብዳቤ ህጋዊነት እንደሌለው ተነግሮኛል።" የሚሉት ወይዘሮ ፅጌ፤ ለመፍትሄው የተሰጣቸው አቅጣጫ፣ የደሀ ደሀ በሚል በድጋሚ ማመልከት እንደሚጠበቅባቸው ነው፡፡ ይህም ለእንግልት እንደዳረጋቸው ነግረውናል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ ቤቶች ፅህፈት ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ፅጌ ከተማ ባለጉዳዮች ላነሷቸው ቅሬታዎች በአንድ ማዕከል አገልግሎት ተገቢውን ምላሽ መስጠታቸውን ገልጸዋል፡፡ "ባለጉዳዮቻችን የኛ የሥራችን አንድ አካል ናቸው፡፡ ቅሬታቸውን በተለያየ አግባብ ቢያነሱም እንደ ተገቢነቱ እያስተናገድን ነው፡፡ የህግ አግባቡ መመሪያው በፈቀደለት ሁናቴ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም በቦታው ላይ ተገኝቶ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ላይ ባለጉዳዮች ላነሱት ቅሬታ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ የሚደረግበት አግባብ እንዳለ ታዝቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከላይ በቤት እጦት ምክንያት ትልቅ እንግልት ውስጥ የነበሩት እናት መፍትሄ እንዲያገኙ ከማስቻል አንፃር የክፍለ ከተማው ቤቶች ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ፅጌ ወረዳ ድረስ በመደወል ጉዳያቸውን አጣርተው ተገቢውን ምላሽ መስጠታቸውን ተመልክቷል፡፡

ወጣት ኤፍሬም ስዩም ይባላል፡፡ "ኤፍሬምና ጓደኞቹ" የተሰኘ ማሕበር



ፎቶ- በገነት ወንድሙ
በባለጉዳይ ቀን አመራሩ የተገልጋይን ቅሬታ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ሲፈታ

በማቋቋም የፈጣን ምግብ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ መቀመጫቸውን በአራዳ ክፍለ ከተማ ያደረጉት እነኤፍሬም የሚሠሩበት ስፍራ ከተፈቀደው ውጪ ዳስ በመጣላቸው 5 ሺህ ብር የቅጣት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡ ይህንን ውሳኔ መነሻ በማድረግ ቅሬታውን ለማቅረብ ወደሚመለከተው የመንግስት ተቋም መምጣቱን ያነሳል፡፡ የመሣሪያ ቦታቸው ለፀሐይ እጅግ የተጋለጠ በመሆኑ ተጠቃሚዎች ምቾት እንዳይነሳቸው፣ ሥራቸውም በፀሐይ ምክንያት እንዳይበላሽ በማሰብ ያደረጉት ስለመሆኑ ወጣት ኤፍሬም ተናግሯል፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት ለማነጋገር በባለጉዳይ ቀን መምጣታቸውንና የክፍለ ከተማው ስራ አስፈፃሚ፣ ምክትል ስራ አስፈፃሚ ብሎም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተገኙበት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ላይ ጥያቄያቸውን ማቅረብ ችለዋል። በተሰጣቸው ምላሽም አሁን ላይ እንደ ከተማ የወረደ አቅጣጫን መሠረት በማድረግ ማንኛውም አካል ስራ እንዲሰራ ከተፈቀደለት ስፍራ ውጪ ዳስ መጣል አልያም ከመስሪያ ቦታ ውጪ ወንበሮችን ደርድሮ ተጠቃሚን ማስተናገድ እንደማይቻል በአራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ወንድሙ ኡመር ተገልጾላቸዋል፡፡

ወይዘሮ አሰለፈች ቦኮ ይባላሉ፡፡ በየካ ክፍለ ከተማ በተለምዶ 41 ኢየሱስ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናቸው። የመሬት ግብር ለመክፈል አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ ወደ ክፍለ ከተማው ገቢዎች ጽህፈት ቤት መምጣታቸውንና ባገኙት አገልግሎት ተደስተው እየተመለሱ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ እንደሳቸው ገለፃ፤ ካለምንም እንግልት ጉዳዬን ፈፅሜለሁ፡፡ በተለይ አመራሩ በባለጉዳይ ቀን የሰዎችን ጥያቄ ለመመለስ የሚሄድበትን ትህትናን የተላበሰ መስተንግዶ አድንቀዋል፡፡

ወይዘሮዋ፤ ከዚህ ቀደም የማመናጨቅና የማንገላታት ሁኔታ ይስተዋል ነበር። አሁን ላይ በዚህ ልክ ተስተካክሎ ማየታቸው አስደስቷቸዋል፡፡ ባለሙያው እራሱ ትህትና በታከለበት አግባብ "ጉዳዩ ምንድነው?" በማለት የሚጠይቅበት የሥራ ሥነ ምግባር እየተፈጠረ መጥቷል። አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ስለመያዛችን ግልፅ በሆነ መንገድ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በፊት የነበረው 'ጉዳዬ በስንት ጊዜ ያልቅ ይሆን?' ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ለመምጣቱ ዋነኛ ምክንያት ሰርቶ የሚያሰራ አመራር በስፍራው መገኘት መቻሉ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ መሰረት ያየሽ ይባላሉ፡፡ በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 2 ነዋሪ ናቸው፡፡ "የእድር ቤታቸው በልማት ፈርሶባቸው ተለዋጭ እንደሚሰጣቸው ቢነገራቸውም ላልተገባ ምልልስ መዳረጋቸውን ገልፀውልናል። ክፍለ ከተማው ጥያቄያችን ትክክል ስለመሆኑ ቢረዳም ጉዳዩን ግን ለማስፈፀም ዘግይቶብናል፡፡ ጉዳዩን በቅርበት የያዘው የክፍለ ከተማው ቤቶች ጽህፈት ቤትም በምላሹ ምንም አይነት ውክልና የሌላቸው የእድር አባላት መጥተው ጉዳዩን ማስፈፀም አይችሉም፡፡ ይልቁኑም ህጋዊ ውክልና ያላቸው ብሎም የእድር ሰብሳቢ የሆኑ ህጋዊ አካላት ናቸው ከምን ደረሰ ብሎ የመጠየቅ ብሎም የማስፈጸም መብት ያላቸው" የሚል ምላሽ እንደሰጣቸው ገልጸውልናል፡፡

አቶ ማሙሽ አግዴ በየካ ክፍለ ከተማ ቤቶች ጽህፈት ቤት የይዞታ ማስተካከል ቡድን መሪ ናቸው፡፡ በርካታ ቁጥር ያለው የኅብረተሰብ ክፍል የመሬት ነክ ጉዳዮችን ይዞ ይመጣል፡፡ ቅሬታዎች የሚነሱባቸው አግባቦች የተለዩ መሆናቸውን ተከትሎ በየዘርፉ ያለ አመራር መፍትሄ እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ "እንደ ክፍለ ከተማችን ተጨባጭ ሁኔታ በባለጉዳይ ቀን አመራሩ መስክና ስብሰባዎችን ከማድረግ ይልቅ ለሚነሱ ቅሬታዎች መፍትሄ የሚሰጥበት አግባብ ሰፊ ነው። የኮሪደር ልማት ሥራዎች በስፋት የሚከናወንበት አካባቢ መሆኑን ተከትሎ አመራሩ ጊዜውን በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል እያገለገለ ይገኛል፡፡ በተለይም ከስራ ሰዓት ውጪ ባሉ ቀናት ጭምር የማኅበረሰቡን መረጃዎች በማደራጀት በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል" ሲል ተናግሯል፡፡

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ

### በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወደ አዲስ መሶብ ከገቡ አገልግሎቶች የቤቶች ልማትና አስተዳደር እና ቤቶች ኮርፖሬሽን ስራዎች ተጠቃሽ ናቸው

**የቤቶች ልማትና አስተዳደር**

1. የአከራይ ተከራይ ምዝገባ ማድረግ
2. የአከራይ ተከራይ ውል ማደስ ወይም ማቋረጥ
3. በኪራይ ቤት የተመደበላቸዉን አካላት ዉል የማዋዋል አገልግሎት፣
4. የቤት ቅይይር ጥያቄን ምላሽ የመስጠት አገልግሎት፣
5. ለተነሺዎች ምትክ ቤት የመመደብ አገልግሎት
6. ከተላለፉ 5 ዓመት በሞላቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች አምስት ዓመት ስለመሙላቱ ማስረጃ የመስጠት አገልግሎት
7. የዉሃና የመብራት ማስገባት የፍቃድ አገልሎት
8. የኪራይ ውል ማደስ ወይም ማቋረጥ አገልግሎት፣
9. የመንግስት ቤት ስም ዝውውር አገልግሎት
10. የቤት እድሳትና ጥገና ጥያቄ አገልግሎት፣
11. የአገልግሎት ዓይነት ለውጥ ጥያቄ አገልግሎት
12. የመንግስት ቤትን ማካፈል ጥያቄ አገልግሎት

**ቤቶች ኮርፖሬሽን**

1. የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ማስተላለፍ
2. የንግድ ቤት በሽያጭ ማስተላለፍ

**ምንጭ፡- የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ማህበራዊ ትስስር ገጽ**

# ተረጅነትን የረቱ እጆች





ፎቶ- በገነት ወንድሙ

በሴፍትኔት ተደራጅተው መስሪያ ቦታ ተሰጥቷቸው እየሰሩ ያሉ ተጠቃሚዎች

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ወይዘሮ እመቤት ሰለሞን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሳለሚያ አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ በምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) መርሃ ግብር ታቅፈው ለሦስት ዓመታት ቆይተዋል፡፡ በክፍለ ከተማው ወረዳ 14 የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው መስራት ከጀመሩ ደግሞ ጥቂት ጊዜያት ሆኗቸዋል። ሥራ ሲጀምሩ ፕሮጀክቱ ከሚከፍላቸው ደመወዝ የሚቆጥቡትን እና ድጋፍ የተደረገላቸውን ገንዘብ ተጠቅመው የሴት ልብሶችን (ፒጃማ፣ ሻርፐ እና የውስጥ ልብሶችን) ሲሸጡ ነው ያገኘናቸው፡፡

በመርሃ ግብሩ ታቅፈው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ልጆቻቸውን ለማሳደግ መስዋዕትነት እንደከፈሉ የተናገሩት ዓይናቸው በእንባ ተሞልቶ፣ ድምፃቸው ሲቃ እየተናነቀው ነው። "ባለቤቴ ተሯሩጦ ከሚሠራው የሚገኘው ገቢ ቤተሰብ ለማስተዳደር አያስችልም ነበር፡፡ ለልጆቼ ዳቦ መግዣ ሰው ቤት እንጀራ ጋግሬያለሁ፣ ጉሊት ጎመን ቸርችሬያለሁ፣ ባህላዊ ጌጣጌጦችን ሠርቼ ሸጫለሁ፤ የቻልኩትን ያህል ሥራ እሠራ ነበር፡፡ የማስበው ድሮ የመጣሁበትን የቤተሰቦቼን የተሻለ የሕይወት ታሪክ ሳይሆን፣ ልጆቼ የእኔን ዓይነት ኑሮ እንዳይኖሩና ተምረው ጥሩ ደረጃ እንዲደርሱ ነው" ሲሉ የቅርብ ጊዜ ትውስታቸውን ገለጹልን፡፡ ከነበረባቸው ኢኮኖሚያዊ ጫና በተጨማሪም ተሸክመው ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲንከራተቱ ወድቀው የዲስክ መንሸራተት አጋጥሟቸው እንደነበርም ነግረውናል፡፡

በምግብ ዋስትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጋቸው ያለፉትን ሕይወት "ነበር" ብለው እንዲያወሩ አድርጓቸዋል። በሴፍቲኔት ታቅፈው በየወሩ ከሚከፈላቸው ገንዘብ ከልጆቻቸው ጉሮሮ ቀንሰው የቻሉትን የሴቶች ልብሶችን በየቢሮውና በየመኖሪያ ቤቱ እየወሰዱ በሁለት ወር እንዲከፍሏቸው ይሸጡ ነበር፡፡ "በእጅ ሰጥቶ በእግር ልመና" እንዲሉ ብሩን ለመቀበልም ይቸገሩ ነበር፡፡ ከነበሩበት ውጣ ውረድ እና ችግር ለመውጣት የሚያስችላቸው መሸጫ ሱቅ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህን በተመለከተም፣ "ተሸክሜ ከመንከራተት ወጥቻለሁ፡፡ እረፍት በማግኘቴም ጤናዬ ተስተካክሎ በተሻለ ደረጃ ላይ እገኛለሁ፡፡

**በምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) መርሃ ግብር ታቅፈው ወደ ሥራ የገቡ ዜጎች የወደፊት ሕልማቸውን ለማሳካት በር ተከፍቶላቸዋል። "አይቻልም" የሚለውን መንፈስ እንደሚቻል ማሳየት ችለዋል**

እንደበፊቱ ልጆቼን ምን እመግባቸዋለሁ ብዬ አልጨነቅም፡፡ በዕለት በማገኘው ገቢም ዳቦ ገዝቼ እገባለሁ፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፤ በዚህ ሱቅ ሠርቼ በቅርብ ጊዜ እለወጣለሁ፡፡ ከዝቅታ ከፍታም እንዳለ አምናለሁ" ሲሉ ያሉበትን ሁኔታና ተስፋቸውን ጭምር ነግረውናል፡፡

አቶ ሰለሞን ተስፋዬ በተመሳሳይ ከነበሩበት አስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ መላቀቅ መቻላቸውን ያነሳሉ፡፡ "የምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) ፕሮግራም ባለውለታዬ ነው" ሲሉም ነው የገለጹት፡፡ ኑሮን ለማሸነፍና ስድስት ቤተሰቦቻቸውን ለማስተዳደር ጫማ ሥራ ተቀጥረው ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ይህም የሰቀቀን ኑሮ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ በፕሮግራሙ መታቀፋቸው ከዚህ በፊት በሚሰጣቸው ብር ቤተሰቦቻቸውን ማስተዳደር ችለዋል፡፡ አሁን ደግሞ የመሥሪያ ቦታ እና የድጋፍ አገልግሎት አግኝተው የግላቸውን "ሲቲና፣ ሰለሞንና ጓደኞቻቸው ቆዳና የቆዳ ውጤቶች የሽርክና ማህበር" በሚል ተደራጅተው እንዲሠሩ በተፈጠረላቸው ዕድል ጫማ፣ ቦርሳና ቀበቶ በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ቀደም ሲል ጫማ ቤት ተቀጥረው ሲሠሩ በነበረበት ወቅትም በነፃነት ለመሥራት ሲቸገሩ መቆየታቸውን ገልጸው፣ "በአሁኑ ወቅት ቤት ኪራይ ሳልከፍል የራሴ የምለውን ሥራ በመሥራቴ ደስተኛ ነኝ፤ ራሴን እያሻሻልኩ እንድሄድም መንገድ ከፍቶልኛል" ይላሉ።

ተቀጥረው ይሠሩ በነበረበት ወቅት ስድስት ቤተሰብ ማስተዳደር ቀላል እንዳልነበረ የነገሩን አቶ ሰለሞን፤ ለግለሰብ ተቀጥረው ሲሠሩ በነበሩበት ጊዜ የነበረባቸው ጭንቀት ተወግዶ እፎይታን አግኝተዋል፡፡ ምንም እንኳን በሴፍቲኔት መሥሪያ ቦታ ተሰጥቷቸው ሥራ ከጀመሩ ጊዜው አጭር ቢሆንም ቤተሰቦቻቸውን እንዲመግቡ፣ የጀመሩትን ሥራ አስፋፍተው ወደፊትም የጫማ ፋብሪካ የመክፈት ሕልማቸውን እውን እንዲያደርጉ መነሻ እንደሆናቸው በደስታ ነግረውናል፡፡

"ማንኛውም ወጣት ዝቅ ብሎ በመሥራት ራሱን ከፍ አድርጎ ማሳየት መቻል አለበት" የሚሉት አቶ ሰለሞን፤ ሰዎች ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ እንዳያሳልፉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሥራና ክህሎት ቢሮ የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ተወካይና የሕብረተሰብ ተሳትፎ ቡድን መሪ አቶ አብርሃም እልፌ በከተማ ደረጃ ሴፍቲኔት መቼ እንደተጀመረ፣ የተቋቋመበት ዓላማ እንዲሁም ምን ያህል የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ እንዳደረገ የዝግጅት ክፍላችን አነጋግረናቸዋል፡፡

አቶ አብርሃም በሰጡት ምላሽ፤ መርሃ ግብሩ በ2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረ ሲሆን፤ ዓላማው በከተማዋ በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ ዜጎችን ከተረጂነት ወደ ምርታማነት እንዲሸጋገሩና የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ነው፡፡ አለፍ ሲልም ሌሎችንም እንዲጠቅሙ ማስቻል ነው፡፡

በዚህ መሠረትም በዘንድሮው ዓመት ባለ አራት ወለል አራት ሕንፃዎች እና 19 ሼዶች ተገንብተዋል። በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በመለየትም ተሰጥተዋል፤ ተጠቃሚዎቹም ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ በባለ አራት ወለል አራት ሕንፃዎች ላይ 292 ኢንተርፕራይዞች እና 976 በቤተሰብ ተወካይ (አባወራዎችና እማወራዎች) እንዲሁም ከተገነቡት 19 ሼዶች ውስጥ ሁለቱ ሼዶች ለሌላ አገልግሎት የዋሉ ሲሆን፣ በ17 ሼዶች 17 ኢንተርፕራይዞች እና 170 በቤተሰብ ተወካይ ተሰማርተው እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በግንባታ፣ በከተማ ግብርና፣ በንግድ፣ በአገልግሎት ዘርፍ ሥልጠናዎችን እንደየዘርፋቸው የወሰዱ ናቸው፡፡

እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሦስት ዓመታት በፕሮግራሙ ታቅፈው የነበሩና በኮሚቴ በመለየት፣ በሕብረተሰቡ በመተቸት፣ በቅሬታ ኮሚቴ ታይተው የተመረጡ ናቸው፡፡ ከዚያም ለእያንዳንዳቸው 600 ዶላር የማቋቋሚያ ድጋፍ ተደርጎላቸው ከተረጂነት ወደ አምራችነት እንዲሸጋገሩ የተደረጉ ናቸው።

እነዚህ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች በአስቸጋሪ ሕይወትና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኙ የነበሩ ናቸው የሚሉት አቶ አብርሃም፤ ከተረጂነት ወደ አምራችነት መሸጋገራቸው የነበረባቸውን ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ጫና በመቅረፍ የ"ይቻላል" መንፈስ እንዲላበሱ ያደርጋቸዋል። ከኢኮኖሚ አንፃር ከሌሎች ሲጠብቁ የነበረውን ራሳቸውን እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ ራሳቸው ተለውጠው ለሌሎችም የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ እስካሁን በተሠሩት ሥራዎችም እነዚህን ለውጦች አምጥተው ተመልክተናል፡፡

መርሃ ግብሩ በከተማ ደረጃ ትኩረት አድርጎ የሚሠራው ቀጥታ ድጋፍ ከማድረግ ባለፈ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ የተለያዩ የድጋፍ ሥራዎች ላይ ነው። የአመለካከት፣ የሕይወት ክህሎት እና ሙያዊ የሆነ ቴክኒካል ሥልጠናዎች ይሰጧቸዋል፡፡ በባለሙያ የተደገፈ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙም ይደረጋል። በዋናነትም ትኩረት የሚደረገው በዘላቂነት ኑሯቸውን በሚለውጡ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ነው፡፡

"በቅርብ ጊዜ የሥራ ዕድል ተመቻችቶላቸው ወደ ሥራ የገቡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ምርታማ መሆናቸው ብቻ በቂ አይደለም" ያሉት አቶ አብርሃም፤ ለምሳሌ እንቁላል ማምረት የጀመሩትን ከሆቴሎችና ነጋዴዎች ጋር ትስስር የመፍጠር፣ ሥራቸውን ይዘው እንዲወጡ ባዛር ማዘጋጀት፣ ለእነሱም ቅድሚያ መስጠት፣ የተለያዩ ባለሃብቶችን በማነጋገርና ከማይክሮ ፋይናንስ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የማመቻቸት፣ ብድር ከወሰዱም በኋላ ከገንዘብ አያያዝ እና ተግባብቶ መስራት እንዲችሉ ሥልጠና የመስጠት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ነግረውናል፡፡

ከግብር ጋር ተያይዞ ስምምነት ሲያደርጉ የእፎይታ ጊዜ እንዲያገኙ ውል እንዳይዋዋሉ የማቆየት ሥራ በመሥራትም ትልቅ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

በምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) መርሃ ግብር ታቅፈው ወደ ሥራ የገቡ ዜጎች የወደፊት ሕልማቸውን ለማሳካት በር ከፍቶላቸዋል፡፡ "አይቻልም" የሚለውን መንፈስ እንደሚቻል ማሳየት ችለዋል። ሁልጊዜ ተረጂ ነን ከሚል አስተሳሰብና ትናንት ከነበሩበት ችግር ወጥተው መስራት እንደሚችሉና አቅም እንዳላቸው ተረድተውበታል፡፡ መስራት መሻገር እንደሆነና ወደፊትም የተሻለ ሕይወት እንደሚኖሩ መሠረት የሚሆናቸው ነው፡፡ ይህ ሲሆን ከራሳቸው አልፈው ሀገራቸውንም ጭምር የሚጠቅሙ ይሆናሉ ብለዋል፡፡

በከተማዋ እየተተገበሩ ካሉ የዜሮ ግብ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ተረጂነት እና ልመናን ዜሮ ማድረግ ነው። ለዚህም በዘንድሮው የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ላይ በአዲስ ከተማ፣ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በየካ እና በቂርቆስ ክፍለ ከተሞች፣ አራት ባለ አራት ወለል የማምረቻ እና መሸጫ ሕንፃዎችን ከዚህ ቀደም በምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) ፕሮግራም ታቅፈው ሲሠሩ ለነበሩ የከተማዋ ነዋሪዎች በማስረከብ ወደ ሥራ መግባታቸው የሚታወስ ነው፡፡

# የጥበብ ማዕድ

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ፊልም፣ የሐሳብና የመጽሐፍ መድረክ፣ የጥበብ አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

"የቼቼላው አባታችን" የተሰኘው መጽሐፍ በዛሬው ዕለት ይመረቃል። መጽሐፉ ለ52 ዓመታት በሕክምናው ዘርፍ በመስራት በርካታ ፕሮፌሰሮችን እና ዶክተሮችን ያፈሩትና የኢትዮጵያ ባለውለታ የሚባሉት ፕሮፌሰር ማለደ ማሩን የሕይወት ታሪክ የሚዳስስ ነው፡፡ የፕሮፌሰሩ የሕይወት ታሪክ በአስተባባሪ ኮሚቴዎች እገዛ በደራሲ ዶክተር ሰለሞን በርሄ ጸሐፊነት መታተሙ ተሰምቷል። መጽሐፉ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ቀበና አደባባይ በሚገኘው የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ማህበር (EPHA) አዳራሽ ተመርቆ ለንባብ ይበቃል፡፡

## የሐሳብና የመጻሕፍት መድረክ

"ሀገር በቀል የሥነ-ፈለክ ምርምር" በሚል ርዕስ በዛሬው ዕለት የሐሳብና የመጻሕፍት ውይይት ይደረጋል። በዕለቱም "የሰማይ ምስጢር፣ አስትሮኖሚ፣ አስትሮ-ፎቶግራፊ እና ባሕላዊ ዕውቀት" በሚል ርዕስ የዘርፉ ልሂቃን መነሻ ሐሳብ አቅርበው ውይይት ይደረጋል፡፡ ውይይቱ 4 ኪሎ ኢክላስ ሕንፃ ዋልያ መጻሕፍት አዳራሽ ዛሬ ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ እንደሚካሄድ ተገልጿል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የጥበብ አውደ ርዕይ

"ኩይሳ" (KUYISA) የተሰኘው የታምራት ገዛኸኝ አዳዲስ የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎች አውደ ርዕይ በትናንትናው ዕለት ለእይታ በቃ፡፡ ይህ አውደ ርዕይ ሰዓሊና ቀራጺ ታምራት ገዛኸኝ "ቆሻሻ የጥበቤ ጡብና ስሚንቶ ነው" በሚል ቃል ከተለያዩ የወዳደቁ ቁሳቁሶች የሠራቸውን ልዩ የጥበብ ውጤቶች ለተመልካች ያቀረበበት ነው። አውደ ርዕዩ የሚታየው ብስራተ ገብርኤል፣ ላፍቶ ሞልን አለፍ ብሎ በሚገኘው ሚካኤል ጸጋዬ ክሬቲቭ ስቱዲዮ ነው፡፡

በሌላ ዜና ሴት የጥበብ ባለሙያዎች የስዕል ሥራዎቻቸውን እያቀረቡበት ያለው የስዕል አውደ ርዕይ ከነገ በስትያ ይጠናቀቃል፡፡ ይህ አውደ ርዕይ እየታየ የሚገኘው ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ነው፡፡

እንዲሁም የሚኪያስ አበራ የግል የሥዕል ኤግዚቢሽን በአርታዊ ጋለሪ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ አውደ ርዕይው እስከ መጋቢት 27 ቀን 2018 ዓ.ም የሚቆይ ሲሆን እየታየ የሚገኘው ደግሞ በሌ ብሪቲሽ ኢንተርናሽናል ስኩል አጠገብ ኬኬር ሆምስ 2ኛ ፎቅ በሚገኘው አርታዊ ጋለሪ ውስጥ ነው፡፡

## ፊልም

"ለፋሲካ ሌሊት" የተሰኘው ፊልም፣ ትናንት ምሽት ተለቀቀ፡፡ ፊልሙ የተዘጋጀው በዳግም ሲሳይ ሲሆን በናሆም መልቲሚዲያ አማካኝነት ለህዝብ ደርሷል፡፡ ፊልሙ ሁለት ጥንዶች በፋሲካ ዋዜማ ሌሊት የሚያሳልፉትን አስገራሚና ልብ አንጠልጣይ ታሪክ የሚተርክ ነው፡፡ ቸርነት ፍቃዱ እና መስከረም አበራን ጨምሮ ወጣትና አንጋፋ የጥበብ ሰዎች ተውነውበታል፡፡ ይህ ፊልም ከዚህ ቀደም የ"European Work in Progress (EWIP)" ፊልም ሽልማት ማግኘቱ ይታወቃል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር


የደጃዝማች ባልቻ ሳፎን ጀግንነት፣ ፍቅር፣ ሰብዓዊነትና መስዋዕትነትን የሚተርከው "ባልቻ አባ ነፍሶ" ታሪካዊ ቴአትር ነገ በ8:00 ሰዓት በአዲስ አበባ ቴአትር እና ባህል አዳራሽ እንደሚመረቅ ተገልጿል። ባልቻ አባ ነፍሶ ታሪካዊ ቴአትር ከማዝናናት በላይ ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከርና ትውልዱ ታሪኩን እንዲያውቅ ለማድረግ የሚረዳ የጥበብ ስራ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በደራሲ ብርሃኑ ዘሪሁን ተደርሶ በተሻለ አሰፋ (ዶ/ር) አዘጋጅነት ለመድረክ የተሰናዳው ባልቻ አባ ነፍሶ ታሪካዊ ቴአትር አንጋፋና ወጣት ተዋንያን እንደተሳተፉበትና ከአራት ወር በላይ በልምምድ እንደቆየ ታውቋል።

# የቁጥር ጨዋታ


## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል። በክበቡ ተቃራኒ በኩል ያሉ ሁለት ቁጥሮች ድምር ሁልጊዜ እኩል (24) ነው። ይህም ማለት 11 + 13 = 24 ይሆናል። 7 + 17 = 24 ነው። በተመሳሳይ 8 + 16 = 24 ይሆናል። በዚህ ስሌት መሰረት የመጨረሻው 4 + ? = 24 ሲሆን መልሱም 20 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **20** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ጥበብና ጥበበኞችን ያገናኙ ስፍራዎች



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከሰሞኑ በአራዳ ፖርክ የወጣቶች የኪነ-ጥበብ እና የስፖርት ፌስቲቫል ተካሂዷል

**በጊዜው አማረ**

አዲስ አበባ በታሪካዊ ጠቀሜታዋ፣ በባህል ሀብቷና በዓለም የፖለቲካ ማዕከልነቷ የምትታወቅ ከተማ ናት። ሆኖም ለረጅም አመታት የከተማዋ ነዋሪዎችና እንግዶች የሚዝናኑባቸው፣ ጥበባዊ ስራዎች የሚቀርቡባቸውና ንጹህ አየር የሚያገኙባቸው ክፍት የህዝብ መዝናኛ ስፍራዎች እጥረት በጉልህ ይታይባት ነበር።

የከተማዋ የህዝብ ብዛት በፍጥነት እያደገ መምጣቱ፣ ክፍት ቦታዎች ሁሉ ለግንባታ መዋላቸው በአካባቢ ጥበቃና በማህበራዊ መዝናኛ ጉዳይ ትልቅ ስጋት ሆኖ ነበር። ይህም ወጣቶችና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የፈጠራ ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡባቸው የአንፊ-ቴአትርና የህዝብ መዝናኛ ፓርኮች እጥረት እንዲስተዋል አድርጎ ቆይቷል።

አሁን ላይ በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉት የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎች ገጽታዋን ሙሉ በሙሉ ቀይረውታል። ቀደም ሲል ለቆሻሻ መጣያነት ይውሉ የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች ዛሬ ወደ ውብ መናፈሻዎችና ለእግር ጉዞ ምቹ ወደ ሆኑ መንገዶች ተቀይረዋል። ይህም ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለዓይን ማራኪና ለኑሮ ተስማሚ በማድረግ ረገድ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል።

በእነዚህ የልማት ስራዎች ውስጥ ጎልተው የሚታዩት አዳዲስ ፓርኮች፣ ፕላዛዎችና ዘመናዊ የአንፊ-ቴአትሮች የከተማዋን የኪነ ጥበብ ህይወት አድሰውታል። የዘርፉ ባለሙያዎች ስራዎቻቸውን በነጻነትና በክፍት አየር የሚያቀርቡባቸው መድረኮች በመፈጠራቸው፣ ከተማዋ የባህልና የጥበብ መንደር እንድትሆን አቅም የፈጠሩ ናቸው። ይህም ነዋሪው ጥበብን ከአረንጓዴ ልማት ጋር አጣምሮ እንዲያገኝና ማህበራዊ ትስስሩን እንዲያጠናክር ትልቅ እድል ፈጥሯል ይላል፤ የኪነ ጥበብ ባለሙያው ቢተው ዳዊት።

ቢተው ከጓደኞቹ ጋር በመሆን አርቲስት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) ጋር ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የኪነት ማህበር ቢመሰርቱም፣ ቀጣዩ ጉዟቸው ግን በመድረክ እጥረት የታጠረ ነበር። ይህ መሰረታዊ ችግር የጥበብ ስራዎች ለህዝብ እንዳይደርሱና የፈጠራ አቅም እንዲገታ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል።

በወቅቱ የነበረው አማራጭ በየወረዳው በሚገኙና የወጣቶች የስብዕና መገንቢያ ማዕከል ጠባብ ስፍራዎች እና አዳራሾች ብቻ ነበሩ። ቢተው ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደተናገረው፣ እነዚህ ቦታዎች ለልምምድም ሆነ ለዝግጅት ማቅረቢያ እጅግ የተጨናነቁና የማይመቹ ነበሩ። በጠባብ ክፍሎች ውስጥ ተጠጋግቶ መስራትና የድምፅና የብርሃን ቴክኖሎጂ እጥረት የጥበብ ስራዎቹን ጥራት የሚቀንስ ከመሆኑም ባለፈ፣ ባለሙያዎቹ የፈጠራ አቅማቸውን በነጻነት እንዳያወጡ አድርጓቸው ቆይቷል።

ከቦታው ጥበት በተጨማሪ፣ የማዕከላቱ ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችና ለስብሰባዎች ክፍት መሆን ለዘርፉ ባለሙያዎች ሌላው ፈታኝ ሁኔታ ነበር። አንድ የኪነ ጥበብ ቡድን ለሳምንታት የለፋበትን ዝግጅት ለማቅረብ ሲዘጋጅ፣ ቦታው ለድንገተኛ ስብሰባ ወይም ለሌላ የመንግስት ጉዳይ ስለሚፈለግ ዝግጅቱ እንዲሰረዝ ወይም እንዲራዘም ይገደድ ነበር። ይህ በባለሙያዎቹ ስነ-ልቦና ላይ ተስፋ መቁረጥን ይፈጥር፣ ጥበብን እንደ ሙያ አድርገው ለሚሰሩ ወጣቶች ደግሞ መንገዱን አዳጋች ሲያደርግባቸው ቆይቷል።

ዛሬ ግን በአዲስ አበባ ከተማ የታየው ለውጥ ይህንን ታሪክ ሙሉ በሙሉ የቀየረና አዲስ ተስፋ የሰነቀ ሆኗል። ከተማዋ አሁን የውብ ፓርኮች፣ የሰፊ ፕላዛዎችና ዘመናዊ የአንፊ-ቴአትሮች መገኛ ሆናለች። እነዚህ ቦታዎች መዝናኛ ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ ቢተው ያሉ የኪነት ባለሙያዎች በነጻነትና በኩራት ስራዎቻቸውን ለታዳሚ የሚያቀርቡባቸው ድንቅ መድረኮች ናቸው። ዛሬ ላይ ባለሙያዎች መድረክ ፍለጋ መንከራተታቸው ቀርቶ፣ የፈጠራ ስራቸውን ለማቅረብ የሚያስችል ስፍራ ማግኘት ችለዋል።

አዳዲሶቹ የመዝናኛና የጥበብ ስፍራዎች ራሳቸው "ጥበብ" ሆነው

> "አዳዲሶቹ የመዝናኛና የጥበብ ስፍራዎች ራሳቸው 'ጥበብ' ሆነው መገንባታቸው ለከተማዋ ልዩ ድምቀት ሰጥቷታል። ሰዎች በእነዚህ ውብ ቦታዎች ፎቶ እየተነሱና እየተዝናኑ ጥበብን በአካል የሚታደሙበት እድል ተፈጥሯል"

መገንባታቸው ለከተማዋ ልዩ ድምቀት ሰጥቷታል ይላል። ሰዎች በእነዚህ ውብ ቦታዎች ፎቶ እየተነሱና እየተዝናኑ ጥበብን በአካል የሚታደሙበት እድል ተፈጥሯል። አካባቢው ካለው ተፈጥሯዊ ውበትና ዘመናዊ ግንባታ ጋር ተዳምሮ፣ የኪነ ጥበብ ስራዎች ከበፊቱ በበለጠ ማራኪና ለዓይን የሚስቡ ሆነዋል። ይህ ሁነት ከሰሞኑም በአራዳ ፓርክ ተንጸባርቋል፡፡

የአዲስ አበባ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በአራዳ ፖርክ በርካታ የመዲናዋ ወጣቶች የተሳተፉበት የኪነ ጥበብ እና የስፖርት ፌስቲቫል ባካሄደበት ወቅት በኮሪደር ልማቱ የተሰሩ ፓርኮች የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ ወጣቶች የፈጠራ ስራዎቻቸውን በነፃነት የሚያሳዩባቸው የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች መሆናቸው ታይቷል፡፡ ይህም ወጣቶች ተሰጥኦአቸውን እንዲያሳድጉና በዘርፉ ያላቸውን ተወዳዳሪነት እንዲያጠናክሩ ዕድል ሰጥቷል።

ይህ መድረክ ወጣቶች በስፖርት፣ ሙዚቃ፣ በቴአትር፣ በግጥምና በስነ-ስዕል ዘርፎች ያላቸውን ተሰጥኦ ለታዳሚው እንዲያሳዩ ሰፊ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፣ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የጥበብ ፍሬዎችን በአንድ ማዕከል ያገናኘ ልዩ ክስተትም ሆኗል።

በፌስቲቫሉ ላይ የተሳተፉ ወጣቶች ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በሰጡት አስተያየት፤ በመዲናዋ በኮሪደር ልማት የተገነቡ ዘመናዊ የመዝናኛ ስፍራዎች ተሰጥኦቻቸውን በነፃነት እንዲያጎለብቱና ለህዝብ እንዲያቀርቡ ትልቅ እገዛ እያደረጉላቸው መሆኑንና እንደነዚህ አይነት መድረኮች ቶሎ ቶሎ ቢዘጋጁ ፍላጎታቸው እንደሆነ ገልጸዋል። በመድረኩ ስራዋን ለታዳሚያን ያቀረበችው ወጣት መቅደስ ፋሲካው፣ "ቦታዎቹ የድምጽ ጥናት ለማድረግና ለማቅረብ ምቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ቦታዎች ወደ ሌሎች አካባቢዎችም መስፋፋት አለባቸው" ስትል ሃሳቧን ገልጻለች፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ የዘመናዊ-ባህል ቡድን ተጠሪ የሆነው ወጣት ሙዚቀኛ ዘላለም እሸቱ ለአዲስ ልሳን እንደገለጸው፣ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ የተገነቡት አዳዲስ ፓርኮችና አንፊ ቴአትሮች ለኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ትልቅ ዕድል ፈጥረዋል። በተለይም በአራት ኪሎ ፕላዛና በተለያዩ መሰል ስፍራዎች የሙዚቃ ሥራዎቻቸውን ለታዳሚ ማቅረብ መቻላቸው ቦታዎቹ ባላቸው ንፅህናና ማራኪ ውበት ምክንያት ለጥበብ ሥራዎች እጅግ ምቹ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ አድርጓል። እነዚህ ስፍራዎች በዘመናዊ መልኩ መገንባታቸው የከተማዋን ድምቀት ከመጨመሩም ባለፈ፣ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ከሕዝብ ጋር በቀጥታ እንዲገናኙ አዲስ መድረክ ሆኗቸዋል።

ሙዚቀኛው አክሎም፣ የተገኘው ዕድል መልካም ቢሆንም የኪነ-ጥበብ ቡድኖች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ አሁንም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዳሉ አመልክቷል። በተለይም የወጣቶቹን የመስራት አቅም ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም የተደራጁ የልምምድ ቦታዎች ቢመቻቹ፣ የፋይናንስ ድጋፍ ቢደረግና የባህል አልባሳት አቅርቦት ችግሮች ቢፈቱ የኪነ-ጥበብ ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር እንደሚቻልና እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች ከተሟሉ፣ ወጣቶቹ ካላቸው ከፍተኛ የፈጠራ አቅምና አሁን ካለው የመዲናዋ ለኪነ ጥበብ ምቹነት አንፃር ተወዳዳሪ ሥራዎችን ለማቀረብ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጿል።

የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ በበኩላቸው፣ አዲስ አበባ ምቹ፣ ውብና ጽዱ እየሆነች ነው፡፡ በመዲናችን ለሁሉም ማህበረሰብ የመዝናኛ ቦታዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ወደፊትም በእነዚህ ቦታዎች ላይ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን እያዘጋጀን ወጣቶች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁና እንዲዝናኑ ለማድረግ በኮሪደር ልማቱ በተሰሩ የመዝናኛ ስፍራዎች መርሃ ግብሮች እንደሚዘጋጁ ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተከናወኑ የፓርኮችና የአንፊ-ቴአትሮች ግንባታ ለኪነ-ጥበብ ዘርፉ አዲስ ህይወት ሰጥተውታል። ቢተው እንደሚለው፣ ከሰሞኑ አራዳ ፓርክና የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚዬም ያየሁት ከተማዋ ለነዋሪዎቿ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ የምትመችና የጥበብ ማዕከል እየሆነች መምጣቷን ነው። እንዲህ ያሉ የኪነ-ጥበብ መድረኮች ተጠናክረው መቀጠላቸው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ የጥበብ ባለሙያዎችን ለማፍራትና የአዲስ አበባን ብሩህ ገጽታ ለዓለም ለማሳየት ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል።

ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ሳይንሳዊው የውጤታማነት ማረጋገጫ መንገድ

- የስልጠና ውጤታማነት ጥናቶች ሰልጣኞች በእውቀት፣ በስነ ምግባር እና በአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻላቸውን ያመላክታሉ



ፎቶ- በገነት ወንድሙ
በአካዳሚው የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ነፃነት የምሩ ከተለያዩ ተቋማት ለተውጣጡ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ሲሰጡ

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

ለአመራሮች እና ለባለሙያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎችን ውጤታማነትን በጥናት መለየት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት እሙን ነው፤ ምክንያቱም አጋጣሚው ስልጠናው በሰልጣኙ ባህሪ እና በተቋሙ ምርታማነት ላይ ያመጣውን ለውጥ ለመለካት ያስችላልና። እንዲህ ዓይነቱ ሳይንሳዊ ግምገማ፣ አካዳሚዎች የሚሰጧቸው ስልጠናዎች ከተጨባጭ ችግሮች ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ከማረጋገጡም በላይ፣ የመንግስት ሀብትና ጊዜ ውጤት ለሚያመጡ ተግባራት ብቻ መዋሉን የሚያረጋግጥ ወሳኝ መሳሪያ ነው።

የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ፋይዳው ሰፊ ሲሆን፣ በተለይም ስልጠናዎች ከንድፈ-ሀሳብ ወጥተው ወደ ተግባር እንዲቀየሩ በማድረግ ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው። ጥናቱ የአመራሩን የውሳኔ አሰጣጥ ብቃት፣ የባለሙያዎችን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና የተቋማዊ ለውጥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ክፍተትን ለይቶ ለማወቅ ይረዳል። በዚህም መሰረት፣ አካዳሚዎች ስልጠናዎቻቸውን እንደ አንድ ወቅታዊ ክስተት ብቻ ሳይሆን፣ ቀጣይነት ያለው ክህሎትን የሚገነባ እና ለፖሊሲ ማስፈጸሚያ አቅም የሚፈጥር ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት አድርገው እንዲመለከቱት ያስገድዳቸዋል።

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚም የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ማካሄድን በጥብቅ የሚተገብረው ጉዳይ ነው። ለመሆኑ እስከ አሁን ባሉት ጊዜያት ያካሄዳቸው የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ግኝቶች ምን ያመለክታሉ? የሚለውን ነጥብ መፈተሽ የዚህ ፅሑፍ ዓላማ ነው፡፡

አካዳሚው የከተማዋን ውስብስብ እና ዘርፈ-ብዙ የልማት ፍላጎቶች ታሳቢ በማድረግ፣ የስልጠናዎቹን ጥራት በጥናት የመፈተሽ ስራን ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ይታመናል። ከስልጠና በኋላ ያለውን የተግባር አፈጻጸም የሚለካበት የክትትል ስርዓት መዘርጋት፣ የሰልጣኞችን የክህሎት እድገት በዲጂታል መረጃዎች መደገፍ እና ስልጠናዎቹን ከከተማዋ ስትራቴጂካዊ ግቦች ጋር ማጣጣም ላይ አተኩሮ እየሰራም ይገኛል። በተለይም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚስተዋሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን ለመሙላት፣ በጥናት ላይ የተደገፈ የክህሎት ልማት ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የለውጥ መሪዎችን የማፍራት ኃላፊነቱን በላቀ ደረጃ እየተወጣ እንደሚገኝ የአካዳሚው የስራ ኃላፊዎች ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በከተማ አስተዳደሩ ስር ላሉ የመንግስትና የግል ተቋማት አመራሮች እና ባለሙያዎች ስልጠናዎችን ከመስጠት ባለፈ፣ የሰለጠኑ አመራሮች እና ባለሙያዎች በተግባር ላይ የሚያሳዩትን ለውጥ ለማረጋገጥ የስልጠና ውጤታማነት ጥናት ማካሄድን በእቅድ ይዞ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ወይዘሮ ነፃነት የምሩ ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የከተማ አመራር ልማት ዘርፍ የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ነፃነት የምሩ በሰጡን ማብራሪያ፣ አካዳሚው በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ላይ በየዓመቱ የስልጠና ውጤታማነት የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ነፃነት ማብራሪያ፣ የስልጠና ውጤታማነት ጥናት በአብዛኛው የሚያተኩረው ሰልጣኞች የቀሰሙትን እውቀት ወደ ስራ በመቀየር ረገድ ምን ያህል ስኬታማ ናቸው? የሚለውን መለካት ላይ ሲሆን፣ ጥናቱ ተዓማኒነት እንዲኖረውም በተቋሙ ስር ባለ የጥናትና ምርምር ዘርፍ በገለልተኛ አካል ይከናወናል፡፡

ከስልጠና ስራዎች አንፃር ዋና ዋና ተልዕኮዎች የስልጠና ክፍተት የዳሰሳ ጥናት ቀዳሚው ነው ብለው፣ በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ የመንግስትም ሆኑ የግል ተቋማት በሙሉ ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ የስልጠና ክፍተት የዳሰሳ ጥናት ይሰራል ብለዋል፡፡

በተጨማም በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ዓመታዊ የስልጠና መርሃ ግብር የሚዘጋጅ ሲሆን፣ ይህም ስልጠና የሚሰጥባቸው ቀናቶችን የያዘ ብቻ ሳይሆን እንዴት ይሰጣል? የሚለውን ሂደት የሚያሳይና መርሃ ግብሩ ለማንና እንዴት ይሰጣል? ስልጠናዎቹ በመሰጠታቸው ምን ጥቅም ይገኛል? የሚሉ ከአመለካከት፣ ከክህሎት እና ከባህሪ አንፃር የተቃኙ ዓመታዊ የስልጠና መርሃ ግብሮች እንደሚዘጋጁ ነው ያመላከቱት፡፡

ከዚህ በመነሳትም የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክተር የስልጠና ሞጁሎችን አዘጋጅቶ በተለያየ መልኩ ስልጠናዎችን የሚሰጥ ሲሆን፣ በዓመቱ መጨረሻም ሲሰጣቸው የነበሩ ስልጠናዎች ምን ውጤት አመጡ? የሚለውን ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ይዘጋጃል ባይ ናቸው፡፡

በየዓመቱ የዳሰሳ ጥናት ከማድረግ በተጨማሪ በሦስት ዓመት ደግሞ እንደ ማህበረሰብ ወይም እንደተቋም ስልጠናው ምን ፋይዳ አመጣ? የሚለው ይሰራል ብለው፣ በ2016 ዓ.ም ከ2014 እስከ 2016 በተሰጡ ስልጠናዎች ምን ውጤት መጥቷል? የሚል ጥናት ከአፍሪካ ልህቀት አካዳሚ በመጡ ሰዎች መካሄዱን ተናግረዋል፡፡

አመራሩ ስልጠና ከወሰደ በኋላ ከስነ ምግባርና ከክህሎት አንፃር ምን ለውጥ አመጣ? የሚለው ይታያል፡፡ ይህም ከእቅድ ትግበራ አኳያ እቅድ ሲያቅድ፣ የታቀደውን እቅድ ሲከታተል፣ ሲደግፍ፣ ግብረ መልስ ሲሰጥ የነበረውን ክፍተት ከመሙላት አኳያ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ከክህሎት አንፃር ሲዳሰስም የታቀደውን መከታተል ብቻ ሳይሆን የማቀድ ክህሎቱ ምን ይመስላል? እቅድ እንዴት ይታቀዳል? እንዴት ይወርዳል? የሚሉት የእቅድ አዘገጃጀት ምሳሌዎች ሲሆኑ፣ አንድ አመራር ክህሎቶችን እንዴት ይተገብራቸዋል? የሚለውን መሬት ላይ ያለው እውነታ ምንድነው? እያልን እያገናዘብን በምንሰጣቸው ስልጠና አመራሩ ጋር ከስነ ምግባርና ከባህሪ አንፃር ለውጦች መጥተዋል ባይ ናቸው፡፡

አመራሩ ለባለሙያዎች፣ ቡድን መሪዎች፣ ዳይሬክተሮችና አጠቃላይ ተከታዮች እቅድ አዘገጃጀትን መሰረት አድርጎ የሚያደርገው የድጋፍና ክትትል ስራ በእውቀት ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያሳይ ግኝት መኖሩን ጠቅሰዋል፡፡

ከስነ ምግባር አኳያም ቃልን መተግበር መቻሉ ተጠቃሽ ነው ብለው፣ ከልማት፣ ከመልካም አስተዳደር እና አገልግሎት አሰጣጥ አንፃር በየተቋማቱ በመሪነት ላይ ያለው አመራር ብዝሃነትን እና የስነ ምግባር እሴቶችን ከማክበር አንፃር ለውጦች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን አካታች የሆኑ ሰርዓቶች ጭምር እንዲመጡ በርካታ የሪሮርም ስራዎች እንዲሰሩ በማድረግ ረገድ የስልጠና ውጤታማነት ጥናቱ የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው ብለዋል፡፡

በተግባቦት ክህሎት ላይም አመራሩ ከተከታዮቹ ጋር፣ አመራሩ ከበላይ አመራሩ ጋር፣ አመራሩ እርስ በእርስና ከደንበኞች ጋር ያለው የተግባቦት ክህሎት ያለው ተፅዕኖ ተዳሷል፡፡ በዚህ ዙሪያ በአንድ ጊዜ ስልጠና ውጤት የሚጠበቅ ሳይሆን፣ በድግግሞሽ ስልጠናውን የወሰደ ተቋም ወይም ሰው ተመርጦ ለውጤታማነት ስልጠና እደሚጋበዝ ነው ያመላከቱት፡፡ በድግግሞሽ ስልጠናውን የወሰደ ተቋም የረጅም ጊዜና በአጭር ጊዜ ያሳያቸው ለውጦች እንዳሉ በተለይ በተግባቦት ክህሎት ላይ ተገልጋይን ማስተናገድ ማዳመጥ አንዱ ትልቁ ጉዳይ ነው፡፡

እንደ ወይዘሮ ነፃነት ማብራሪያ፣ ብዙውን ጊዜ ሰዎች በኃላፊዎች አንደመጥም፣ ቢያዳምጡንም ከልባቸው ሳይሆን የተለያየ ስራ እየሰሩ ተናገር እናውቀዋለን ወይም ቀጥል እያሉን ነው የሚል ጥቆማ ይሰጣሉ፤ በዚህ ዙሪያም መሻሻል ያለበት አካሄድ አለ ብለዋል፡፡

ከውሳኔ አሰጣጥ ብቃት አኳያም ግራና ቀኙን በደንብ በመመልከት፣ አማራጭ ሃሳቦችን በማቅረብ፣ ወቅቱን የጠበቀ ውሳኔ መስጠት የሚያስችል አቅም መገንባት ተችሏል ባይ ናቸው፡፡

በቡድን መምራትና በማደራጀት፣ ተመሳሳይ ግብ፣ አላማና ተመሳሳይ የሆነ የውጤት መዳረሻ ያላቸው በቡድን የሚሰሩ ሰዎችን በመፍጠር ረገድም እንዲሁ የመጡ ለውጦች አሉ ብለው፣ በግለሰብ ደረጃም ስራዎችን በራሱ እንዴት አቅዶ መስራት እንዳለበት፣ ከሰዎች ጋር እንዴት ነው መግባባት አለብኝ የሚሉና መሰል ተግባራት እንዲያጎለብት ከማድረግ ባለፈ ከባለፈው ጊዜ አንፃር የተሻለ አፈፃፀም ከማምጣት ጀምሮ በአንፃሩ ከነበረው በተሻለ መልኩ እንዲያጎለብት አድርጎታል ሲሉ አክለዋል።

በተረፈ በየዓመቱ የሚጠናው ጥናትም በየጊዜው እየቀረበ ይገመገማል፤ የሚሰጡ ምክረ ሃሳቦች ለከተማ አስተዳደሩ፣ ለአካዳሚው፣ ሰልጣኝ ለሚልኩ ተቋማት፣ ለምክር ቤት፣ ለፐብሊክ ሰርቪስ እና ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተደራሽ ይደረጋል ያሉት ወይዘሮ ነፃነት፣ እነኝህ አካላት በተገኙበት ውጤቱ እንደሚገመገም ነው የገለፁት፡፡

# ልጆች፤ የራሳችሁንና የአካባቢያችሁን ንፅህና የምትጠብቁት እንዴት ነው?




ፎቶ- በገነት ወንድሙ
ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን እና የግል ንፅህናቸውን ሲጠብቁ

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች የግል ንጽህና፣ የአካባቢና የከተማ ፅዳት ወይም ንፅህና እንዴት እንደሚጠበቅና ይኸን ማድረግ ምን ጥቅም እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ? እናንተስ የራሳችሁንና የአካባቢያችሁን ፅዳት ምን ያህል ትጠብቃላችሁ? ያላችሁን አስተያየት ለቤተሰቦቻችሁና ጓደኞቻችሁ እንድታካፍሉ እያልን በዚህ ረገድ ያነጋገርናቸው ልጆችን ተሞክሮ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፤ የዝግጅት ክፍላችን የግል እና የአካባቢያቸውን ንፅህና የሚጠብቁ ልጆችን ልምድና ተሞክሮ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ፡፡

ባምላክ ተመስገን እባላለሁ፡፡ 13 ዓመቴ ነው፡፡ የጥበብ እድገት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነኝ፡፡ የግል ንፅህናዬን እጄንና እግሬን በመታጠብ፣ ጥፍሬን በመቁረጥ፣ ጥርሴን በመቦረሽ፣ ፀጉሬን በመታጠብ እንዲሁም ንጹህ ልብስ በመልበስ እጠብቃለሁ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ማንኛውንም አይነት ቆሻሻ መንገድ ላይ አልጥልም፡፡ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ቅርጫት ላይ አስቀምጣለሁ፡፡

ከዚህ በፊት ጉዳት እንዳለው ሳላውቅ ሙዝ ተመግቤ ልጣጩን ግቢ ውስጥ እጥል ነበር፡፡ አንድ ቀን ታላቅ ወንድሜ “እንደዚህ ሲጣል ሰዎችን አንሸራትቶ ለአደጋ ያጋልጣል” ብሎ በነገረኝ መሰረት በአግባቡ አስወግዳለሁ፡፡ ይህን በማድረጌ ደግሞ ጤናዬ የተጠበቀ ሆኗል። በየጊዜው አያመኝም፡፡ ስለዚህ ልጆች፤ ቆሻሻን በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ መጣል አለባቸሁ፡፡

ሽዋዬ ተሾመ እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ሲሆን የምማረውም በጥበብ እድገት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። በየትኛውም ጊዜና ቦታ በትምህርት ቤትም ይሁን በቤት ውስጥ እጄን በሳሙናና በውሃ የመታጠብ ልምድ አለኝ። ቆሻሻ በየቦታው አልጥልም፤ መጣያ ቅርጫት እስከማገኝ በእጄ እይዘዋለሁ፡፡


ራሴን ንፁህ አድርጌ አካባቢዬን ማቆሸሽ እንደሌለብኝ አምናለሁ፡፡ ራሴን ንፁህ ማድረጌና አካባቢዬን አለማቆሸሼ በንጽህና ጉድለት ከሚመጣ በሽታ እንድጠበቅ፣ ትምህርቴንም በአግባቡ እንድከታተል አድርጎኛል፡፡

ዳግም ሳምሶን እባላለሁ፡፡ ንፅህና ከራስ ይጀምራል፡፡ በዚህም የግል ንጽህናዬን ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ እጠብቃለሁ፡፡ የግል ንፅህናዬን እንደምጠብቀው ሁሉ የምኖርበትን አካባቢ፣ የምማርበትን ትምህርት ቤት፣ በምንቀሳቀስባቸውን ቦታዎች ሁሉ ንፁህ እንዲሆኑ ቆሻሻን በየቦታው ባለመጣል ኃላፊነቴን እወጣለሁ፡፡ ቤተሰቦቼም ስለንፅህና አጠባበቅ ሁልጊዜ ይነግሩኛል፡፡

አቶ ምትኩ ሄርጳ እባላለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የግንዛቤ ስርፀት፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ የአካባቢ ንፅህና ክትትል ዳይሬክተር ነኝ፡፡ ልጆች እጃችሁን፣ ፊታችሁን፣ እግራችሁን፣ ሰውነታችሁን፣ ፀጉራችሁን በመታጠብ፣ ጥርሳችሁን በመቦረሽ እና ንፁህ ልብስ በመልበስ የግል ንፅህናችሁን ትጠብቃላችሁ አይደል? ጎበዞች፡፡ የግል ንፅህናቸሁን እንዲህ ከጠበቃችሁ የምትውሉበትንና የምትኖሩበትን አካባቢ በንፅህና መያዝንም እንዳትዘነጉ፡፡ ይህን የምታደርጉት የምትማሩባቸውንና የምትጫወቱባቸውን ቁሳቁስ በአግባቡ በማስቀመጥ፣ የከረሜላና ብስኩት ወረቀት፣ የፍራፍሬ ልጣጭ፣ የተጠቀማችሁበትን ሃይላንድ እና የመሳሰሉትን ቆሻሻ በአግባቡ የቆሻሻ መጣያ ውስጥ በመጣል ነው፡፡

ልጆች፤ የራሳችሁንም ሆነ የአካባቢያችሁን ንፅህና መጠበቃችሁ ጤናችሁ የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ አካባቢያችሁም ሆነ ከተማችሁ ለእይታ ማራኪ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ቆሻሻን በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ማስወገድ፣ የትምህርት ቤት አካባቢያችሁን አርብ አርብ በሚኖረው መርሃ ግብር ላይ በመሳተፍ ማፅዳት አለባችሁ፡፡ በንፁህ አካባቢ የመማር መብት እንዳላችሁ ሁሉ የአካባቢያችሁን፣ የትምህርት ቤታችሁን እንዲሁም የከተማችሁን ንፅህና የመጠበቅ ኃላፊነትም አለባችሁ፡፡

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እንዲህ ቢሏት አትታይ ፤ እንዲያ ቢሏት አትታይ**

**መልስ፡-** ሀ. ጆሮ

## የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ህይወት የለውም ሌት ቀን የሚሄድ**

ሀ. አውሮፕላን

ለ. ንስር

ሐ. ነፋስ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ተደራሽነትን የማስፋት ጉዞ

**“አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል አቀናጅቶ የማቅረብ መርሃ ግብር በተሟላ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን በኮሪደር ልማት የዘረጋናቸው መሠረተ ልማቶች ወሳኝ ሚና እያበረከቱ ይገኛሉ”**

**የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በደረጀ ታደሰ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2018 በጀት ዓመት የአዲስ ዓመት ስጦታ አድርጎ ለነዋሪው ሕብረተሰብ ያቀረበው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት፤ ተለምዷዊውን አሠራር በዲጂታላይዜሽን በመተካት፣ ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን በመጠቀም፣ የሠራተኛውን የሥራ ሥነ ምግባር በሥልጠናና በተግባራዊ እንቅስቃሴ በማሻሻል፣ ምቹ የሥራ ከባቢን በመፍጠር ሕብረተሰቡ በመንግሥት አገልግሎት ላይ ያለውን እርካታ ከፍ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በዚህም ሰባት ወራትን ባስቆጠረ ዕድሜው ውስጥ በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የቀድሞ ሕንፃ ላይ በሚገኘው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት እንዲሁም በቦሌ ቅርንጫፍ አማካኝነት በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ተገልጋዮች ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ፣ ፈጣን፣ ወጪ ቆጣቢና እርካታን ከፍ የሚያደርጉ አገልግሎቶችን ማቅረብ ተችሏል፡፡

አቶ ዳኜ በቀለ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ነዋሪ ናቸው፡፡ በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት መጥተው ነው ያገኘናቸው። የመጡበት ምክንያት ከተሽከርካሪ ቦሎ ዕድሳት ጋር የተያያዘ መሆኑን በመጠቀም በተቋሙ ያገኙት አገልግሎት በጣም እንዳስደሰታቸው ገልጸዋል፡፡ ሁኔታውንም ሲያብራሩ “የተሽከርካሪ ቦሎ ዕድሳት በየዓመቱ አደርጋለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም በክፍለ ከተማ ደረጃ ነበር የማከናውነው፡፡ እዚያ ብዙ ጊዜ ወረፋ ይበዛል፤ ‘ኔትወርክ የለም፣ መብራት ጠፍቷል፣ ስብሰባ ገብተዋል’ የሚሉ ሰበቦችም በብዛት ያጋጥማሉ፡፡ እዚህ ግን ሁሉ ነገር የተደራጀና ደስ የሚል ነው፡፡ ሠራተኞቹ ከመረጃ ሰጪ ጀምሮ ነገሮች ቀላል እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ በወረፋ እንደአመጣጣችን እንድንገለገል ሥርዓት ተበጅቶለታል፡፡ እኔም በዚሁ መንገድ አልፌ አገልግሎቱን አግኝቻለሁ፡፡ በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ይህን ስሜቴን በአስተያየት ገልጫለሁ” ብለዋል።

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት (ከጳጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም.) እንዲሁም የአገልግሎቱ የመጀመሪያው የሆነው የቦሌ ቅርንጫፍ (ከመስከረም 28 ቀን 2018 ዓ.ም.) ለአገልግሎት ከበቁ በኋላ፣ ከ100 ሺህ ለሚበልጡ ተገልጋዮች የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት ስለመቻላቸው ይፋዊ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ አየለ በቅርቡ ከአዲስ ቲቪ ጋር በነበራቸው ቆይታ “እስከ መጋቢት አጋማሽ 2018 ዓ.ም. ድረስ በዋና መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ አማካኝነት ከ113 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ችለናል” በማለት የደረሱበትን ምዕራፍ ገልጸዋል፡፡ ይህ ቁጥር ማኅበረሰቡ ለዘመናዊና ለዲጂታል አሠራር ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት የሚያሳይ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡




ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ 4ኛውን የቂርቆስ ቅርንጫፍ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ሥራ ሲያስጀምሩ

ወደ አዲስ መሶብ ለአገልግሎት ጎራ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ባገኙት አገልግሎት የተሰማቸው እርካታ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን፣ ከእጅ ንክኪ ውጪ በሆነ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተከናወነ ጥናት ከሰው ንክኪ ውጪ በሆነ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አሠራር የተከናወነ የጥናት ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም ማለት ተገልጋዮቹ ስለአገልግሎቱ የተሰማቸውን እርካታ የሚሞሉት በታብሌት መሆኑ ነው። እሱን መረጃ ወስዶ የሚተነትነው ደግሞ በሶፍትዌር እንደሆነ ከዚህ ቀደም ባቀረብነው ጽሑፍ በስፋት መዳሰሳችን ይታወሳል፡፡ ይህ የጥናት ውጤት፣ የከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት አገልግሎትን ዘመናዊ በሆነ መልኩ ለተጠቃሚው የማድረስ ዕቅዱን ይበልጥ ለማስፋት እንዲበረታ አቅም ሆኖታል፡፡ በዚሁ መሠረት የአዲስ መሶብ አገልግሎትን ተደራሽነት ለማስፋት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ቴዎድሮስ ማስረሻ ናቸው፡፡

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ገለጻ፣ አዲስ መሶብ አገልግሎቱን በጥቂት ማዕከላት ብቻ ገድቦ ለማቆየት አላቀደም። የከተማ አስተዳደሩ በሰጠው ልዩ ትኩረትና ድጋፍ፣ ወደ እያንዳንዱ ነዋሪ ደጃፍ ለማድረስ ሰፊ የቅርንጫፍ ማስፋፊያ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት በሁለት ዋና ዋና ማዕከላት (በዋና መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ) አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከሰሞኑ 3ኛውን የ‘አዲስ መሶብ’ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በልደታ፣ 4ኛውን ደግሞ በቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ስራ አስጀምረዋል፡፡ የልደታው ቅርንጫፍ ባለ ሰባት ወለል ዘመናዊ ማዕከል ሲሆን የተለያዩ የመንግሥት አገልግሎቶችን በአንድ ስፍራ አቀናጅቶ ይዟል። ማዕከሉ የ20 ተቋማትን 112 የተለያዩ አገልግሎቶች በ69 የአገልግሎት መስኮቶች ለተገልጋዮች ያቀርባል። በተጨማሪም 22 ተቋማትን በዲጂታል በይነ-መረብ አስተሳስሯል።

የቂርቆስ ቅርንጫፍ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ደግሞ 20 ተቋማት፣ በ85 የአገልግሎት መስኮቶች፣ 112 የተለያዩ የሕዝብ አገልግሎቶችን በአንድ ስፍራ ለተገልጋይ ያቀርባል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች እነዚህን የአዲስ መሶብ ቅርንጫፎችን ለአገልግሎት ክፍት ሲያደርጉ እንደተናገሩት፣ ሥራው የመንግሥት አገልግሎትን በማላቅ፤ ደላላን፣ ሌብነትን፣ አድሎ እና እንግልትን በማስወገድ፣ ተደራሽነትን እና የዜጎችን እርካታ በማሳደግ፣ በተቋማት መካከል የነበረውን የተበታተነ አገልግሎት በማቀናጀት እንዲሁም ኅብረተሰቡ አገልግሎት ለማግኘት የሚያጠፋውን ጊዜና ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ፍትሐዊ አገልግሎት የሚያሰፍን ይሆናል

የተቀናጁ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የመንግሥት አገልግሎት አፈጻጸም ቁልፍ የከዋኔ መለኪያ እና አጠቃላይ የዜጎች እርካታን እያመጡ፣ አካታች እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማጎልበቻ ሥርአት እየሆኑ ነው። ማዕከላቱ ለአጠቃላይ ተገልጋዩ ማህበረሰብ ምቹ ሲሆኑ፤ በተለይም አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ፣ እንዲሁም ለሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢን የፈጠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የመንግሥት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል አቀናጅቶ የማቅረብ መርሃ ግብር ስኬት እና በተሟላ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን አስቀድመን በኮሪደር ልማት የዘረጋናቸው መሠረተ ልማቶች ወሳኝ ሚና እያበረከቱ እንደሆነም አብራርተዋል።

ተቋሙ የተገልጋዩን ፍላጎት ለማሟላት እና የተደራሽነት አቅሙን ለማስፋት እየሠራባቸው ከሚገኙ አዳዲስና ዘመናዊ የአሠራር ስልቶች መካከል በአውቶብሶች አማካኝነት ተንቀሳቃሽ አገልግሎትን መተግበር ይጠቀሳል፡፡ አቶ ቴዎድሮስ ማስረሻ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ የተቋሙ ሌላው አስደናቂ ፈጠራ የተንቀሳቃሽ አውቶብስ አገልግሎት ነው። ይህ አገልግሎት በተለይ ከአካባቢያቸው ተንቀሳቅሰው ቢሮ መምጣት ለማይችሉ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና በሥራ ለተጠመዱ ዜጎች ትልቅ እፎይታ ይዞ የሚመጣ ነው። አገልግሎቱ የሚሰጠው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በተገጠመላቸው አውቶብሶች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የሙከራ ትግበራው ተጠናቅቆ በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ሙሉ ሥራ ይገባሉ።

ኃላፊው አክለው እንዳብራሩት፣ በእነዚህ አውቶብሶች አማካኝነት በድምሩ 46 የአገልግሎት ዓይነቶች ለተገልጋዮች የሚቀርቡ ይሆናል። ከእነዚህ መካከልም የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት፣ የንግድ ፈቃድ ማውጣትና ማደስ፣ የተሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ እና የቦሎ ዕድሳት፣ የገቢዎችና የታክስ አገልግሎቶች፣ የፋይዳ (ብሔራዊ መታወቂያ) ምዝገባ እንዲሁም የጤና እና የመንገድ ፈንድ አገልግሎቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ። ባለሙያዎች ተለይተው፣ ሥልጠና ወስደው ለሥራ ተዘጋጅተው እየተጠባበቁ ነው፡፡ በአውቶብሶቹ የሚቀርበው አገልግሎት በየክፍለ ከተማውና በየወረዳው የሚዘዋወሩበት ግልጽ የመርሃ ግብር ለሕዝብ ይፋ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ተገልጋዩ አውቶብሱ መቼ ወደ ሰፈሩ እንደሚመጣ ቀድሞ እንዲያውቅ ይረዳዋል።

ማዕከላቱ የተገልጋዩን እንግልት ለመቀነስ የተራዘመ የአገልግሎት ሰዓትን ለሥራ ይጠቀማሉ፡፡ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት ድረስ ያለማቋረጥ አገልግሎት ይሰጣሉ። በተጨማሪም የሥራ ሰዎችንና በሳምንቱ ቀናት የማይመቻቸውን ዜጎች ታሳቢ በማድረግ ቅዳሜ ግማሽ ቀን (እስከ ቀኑ 6፡30) አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ይህ የአሠራር ልምድ እና መርህ ተቋሙ በቅርቡ በሚከፍታቸው ቅርንጫፎችም ተግባራዊነቱ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ ለቅርንጫፎቹ የተቀጠሩ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ አየር መንገድ አቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ እየሠለጠኑ ይገኛል። ሥልጠናው በዋናነት የሚያተኩረው የደንበኞች አያያዝ፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ የተግባቦት ክህሎትና ሙያዊ ሥነ ምግባር ላይ ነው። ይህን ጉዳይ አቶ ቴዎድሮስ “አገልግሎታችን ከሙስና የጸዳ፣ ፈጣንና ፍትሐዊ እንዲሆን የሠራተኞቻችን ዝግጁነት ወሳኝ ነው” ሲሉ ገልጸውታል።

አዲስ መሶብ ከአካል ቅርንጫፎችና ከተንቀሳቃሽ አውቶብሶች ባለፈ፣ አገልግሎቱን ወደ ሞባይል መተግበሪያ (Mobile App) ለማሸጋገር ዝግጅቱን እያጠናቀቀ እንደሚገኝ አቶ ቴዎድሮስ አሳውቀዋል። ዜጎች በቤታቸው ሆነው በስልካቸው ጉዳያቸውን መጨረስ የሚችሉበት ይህ መተግበሪያ፣ አገሪቱ የያዘችውን የ“ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030” ስትራቴጂ ለማሳካት የጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለግላልም ብለዋል።

በአጠቃላይ አዲስ መሶብ ስሙ እንደሚገልጸው፣ የተበታተኑ የመንግሥት አገልግሎቶችን በአንድ “መሶብ” ውስጥ አሰባስቦ ለዜጎች በክብር እያቀረበ ይገኛል። የቅርንጫፎች መስፋፋት፣ የተንቀሳቃሽ አውቶብሶች ሥራ መጀመርና የዲጂታል መተግበሪያዎች መበልጸግ አዲስ አበባን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም ወደ ዘመናዊ የአገልግሎት ሥርዓት የሚያሸጋግር ትልቅ ተሞክሮ ነው። ተቋሙ የጀመረውን ይህንን የለውጥ ጉዞ አጠናክሮ በመቀጠል ለዜጎች እርካታና ለአገር ዕድገት የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወጣ ይጠበቃል።

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ


# አርሶ አደሮችን ያማከሉ የኢኮኖሚያዊ እድገት በሮች

- **በቀደሙት ጊዜያት በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ከተፈናቀሉ አርሶ አደሮች መካከል 160ዎቹን ወደ ኢንቨስትመንት ለማስገባት እየተሠራ መሆኑ ተመላክቷል**

**በይግለጡ ጓዴ**







ፎቶ- በገነት ወንድሙ

በአዲስ አበባ ከተማ በአርሶ አደሮች ከለሙ የከተማ ግብርና ስራዎች በጥቂቱ



አርሶ አደር ለማ ሳህሌ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 ነዋሪ ናቸው። በልማት ምክንያት መሬታቸው ተወስዶባቸው ለከፋ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠው ለዓመታት ቆይተዋል። ከበርካታ የእንግልት ዓመታት በኋላ መሬታቸው ተመልሶላቸው በእንስሳት መኖ ማቀነባበር ዘርፍ ተሰማርተዋል። በዚህም ውጤታማ ሆነዋል፤ አሁን ደግሞ በመንገድ መብራት ፖል እና የድሬኔጅ መስመር ቱቦ ማምረት ሥራ ለመሰማራት በሂደት ላይ ናቸው።

በተመሳሳይ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር በለጠ ፍቅሬ በልማት ምክንያት መሬታቸው ተወስዶባቸው ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ተጋልጠው ነበር። አርሶ አደር በለጠ አሁን የይዞታ መሬታቸው ተመልሶላቸው በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች ተሳታፊ ሆነዋል።

አርሶ አደር በለጠ በእንስሳት ማድለብ፣ በእጽዋት ልማት እና በመናፈሻዎች ውስጥ በሚሰጥ የመዝናኛ አገልግሎት ዘርፎች ተሰማርተዋል። ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ኮሚሽን ያገኟቸው የተለያዩ ድጋፎች ደግሞ ለውጤታማነታቸው መሠረት ሆነዋቸዋል።

ወደ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚገቡ አርሶ አደሮች የብድር አቅርቦት፣ የመስሪያ እና የመሸጫ ቦታዎች እንደተመቻቹ በመጠቆም፤ በወረዳ፣ በክፍለ ከተማ እና በኮሚሽኑ የሚሰጡ ድጋፎች አበረታች መሆናቸውን አርሶ አደሩ ተናግረዋል።

በፊት ለአርሶ አደሩ ይሰጥ የነበረው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን አንስተው፣ ያመርቱበት የነበረውን መሬታቸውን በልማት ምክንያት ተቀምተው ለተለያዩ ችግሮች ተጋልጠው እንደነበር አርሶ አደር በለጠ ጠቁመዋል። ከለውጡ ወዲህ ግን ለአርሶ አደሮች የተለያዩ ማበረታቻዎች ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ መግባታቸው ዳግም የተወለዱ ያህል ስሜት እንደተሰማቸው ተናግረዋል።

አርሶ አደር ዳኜ ጌታሁን ለረጅም ጊዜ በእርሻ ሥራ ይተዳደሩበት የነበረው መሬታቸው በልማት ምክንያት በመወሰዱ ለችግር ተዳርገው እንደነበር ያወሳሉ። ከረጅም ጊዜ ችግር እና እንግልት በኋላ የአርሶ አደር ዳኜ እና የሌሎች የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን ችግር የተመለከተው የከተማ አስተዳደሩ፣ የእንስሳት እርባታና የልህቀት ማዕከል በመገንባት የልማት ተነሺዎችን መልሶ በማቋቋም፤ ድጋፍ እና ሥልጠና በመስጠት ከሌሎች የልማት ተነሺዎች ጋር ተደራጅተው በዶሮ እርባታ ዘርፍ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

በዚሁ ማዕከል የዶሮ እርባታ ሼድ እና ብድር ተመቻችቶላቸው ወደ ሥራ የገቡት አርሶ አደር ዳኜ እና ጓደኞቻቸው በዶሮ እርባታ እና እንቁላል ዘርፍ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ተጠቃሚ ሆነዋል። አንድነት የዶሮ እርባታ እና እንቁላል ሽያጭ የሕብረት ሥራ ማህበር በ15 አባላት በመደራጀት ወደ ሥራ ገብተዋል።

በእርባታ ማዕከሉ በዶሮ እርባታ ዘርፍ ሦስት ማኅበራት በክላስተር ተደራጅተዋል። በዶሮ እርባታ ዘርፍ 11 ሼዶች ይገኛሉ። በአንድ ሼድ ውስጥ ከ3 ሺህ 200 በላይ የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች ያሏቸው እነ አርሶ አደር ዳኜ በቀን 2 ሺህ 900 እንቁላል ይሰበስባሉ።

በቀደመው ሥርዓት በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች መሬት በልማት ምክንያት በመወሰዱ ለኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች ተጋልጠው እንደነበር አይዘነጋም። ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በመንግሥት በኩል የተለያዩ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸው ይታወሳል። የአርሶ አደሮችን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከማድመጥ ጀምሮ ለችግር የተጋለጡትን መልሶ የማቋቋም ሥራ ተሠርቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ አርሶ አደሮች በስፋት ሲጠይቁት የነበረውን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲያገኙ መደረጉ የለውጡ ትሩፋት መሆኑን በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየታቸውን የሰጡን አርሶ አደሮች ተናግረዋል። ምንም ገቢ የሌላቸውን አርሶ አደሮች መሠረታዊ ፍጆታቸውን ከመሸፈን ባለፈ የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ መደረጉም ይታወሳል።

የከተማ ዙሪያ አርሶ አደሮች ከከተማዋ መስፋፋትና ከገበያው ቅርበት የተነሳ በርካታ የኢኮኖሚ ጥቅሞች አሏቸው። እነዚህን ዕድሎች በብቃት በመጠቀም ኑሯቸውን መለወጥ የሚችሉባቸው ጉዳዮች ዘርፈ-ብዙ ናቸው። አርሶ አደሮች ምርታቸውን ረጅም ርቀት ሳይጓዙ በዝቅተኛ የትራንስፖርት ወጪ ለተጠቃሚዎች ማድረስ ይችላሉ። እንደ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ወተትና እንቁላል ያሉ ቶሎ ሊበላሹ የሚችሉ ምርቶችን በትኩስነታቸው ለገበያ ማቅረብ እንደሚችሉና ደላላ ሳያስገቡ በቀጥታ ለሸማቾች ማኅበራት፣ ለሆቴሎች እና ለሱፐርማርኬቶች በማቅረብ የተሻለ ትርፍ ማግኘት ይችላሉ።

የመሬት ስፋት እየቀነሰ በሚሄድበት የከተማ ዙሪያ አካባቢ በትንሽ መሬት ብዙ ምርት የሚሰጡ ዘዴዎችን መጠቀም ትልቅ ዕድል ነው። የከተማን ቆሻሻ ውኃ በማከም ወይም የከርሰ ምድር ውኃን በመጠቀም በመስኖ ልማት በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ በማምረት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። አርሶ አደሮች ምርትን በጥሬው ከመሸጥ ይልቅ እሴት በመጨመር የተሻለ ገቢ ማግኘትም ይችላሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የአርሶ አደር ማቋቋምና ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ረጋሳ ባይሳ፤ ከዚህ በፊት አርሶ አደሮች መብታቸው ተከብሮ ተገቢውን አገልግሎት ሲያገኙ እንዳልነበር በማንሳት፣ ይባስ ብሎ የይዞታ መሬታቸው በልማት ተወስዶባቸው ለተለያዩ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠው መቆየታቸውን ተናግረዋል።

ከለውጡ በኋላ ለአርሶ አደሮች በተሰጠው ትኩረት መመሪያ 20/2013 በማዘጋጀት አሠራር ተዘርግቶ አርሶ አደሩ የራሱ ይዞታ ላይ የማልማት ቅድሚያ እንዲሰጥ መደረጉን ጠቁመው፣ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የአርሶ አደሮችን መብት ለማስከበር በትኩረት መሥራት መቻሉን ገልጸዋል። በዚህም በቅድሚያ አርሶ አደሮቹ በራሳቸው ይዞታ ላይ መብታቸው እንዲከበርላቸው ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው መደረጉን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ረጋሳ ገለጻ፣ ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መብት እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል። መብት ከተፈጠረላቸው በኋላም ካርታቸውን በመያዝ አርሶ አደሮች በተቀመጠው መመሪያ መሠረት ወደ ኢንቨስትመንት ተሰማርተዋል። በትምህርት ቤት፣ ጤና፣ በመኖ ማቀነባበር፣ በግብርና ልማት እና በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችም ተሰማርተዋል።

አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዳገኙ፣ ብድር እንደተመቻቸላቸው እና ሙያዊ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። በዚህም መሠረት 160 አርሶ አደሮችን ወደ ኢንቨስትመንት ለማስገባት እየተሠራ ነው፤ እስከ አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ የገቡት 10 ሲሆኑ፣ 29ኙ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ናቸው። 149 ደግሞ በከንቲባ ጽሕፈት ቤት እና በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ መረጃቸው እየተጣራ እንደሚገኝ አቶ ረጋሳ ገልጸዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ለአካባቢ ጥበቃ መሠረት የመጣል አብነቶች

- **በዘንድሮው በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት በትምህርት ቤቶች 520 የአካባቢ ጥበቃ ክበባት ተቋቁመዋል**

**በለይላ መሐመድ**



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት በትምህርት ቤታቸው የጓሮ አትክልት በመንከባከብ ላይ

ይስሐቅ ማቲዎስ በወይዘሮ ቀለመወርቅ ጥሩነህ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አምባሳደር በመሆንም እየሠራ ይገኛል፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባል ሊሆን የቻለበት ምክንያት፤ ወደፊት የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋች መሆን ስለሚፈልግ እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግሯል፡፡

ተማሪ ይስሐቅ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የዚህ ክበብ አባል በመሆን ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል፡፡ "ለአካባቢዬ የተለየ ፍቅር አለኝ፡፡ ጽዱና አረንጓዴ ነገሮችን ማየት ስለሚያስደስተኝ ተክሎችን መንከባከብ እወዳለሁ፡፡ ክበቡም በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ አንዱ የጽዳት ሥራ ነው፡፡ ሁልጊዜ ዓርብ በክበቡ አባላት መሪነት አጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ የሚሳተፍበት ግቢውን የማጽዳት ሥራ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም የቆሻሻ መጣያ ቅርጫቶችን በማስቀመጥ ተማሪዎች ቆሻሻን በየቦታው እንዳይጥሉ፣ በጽዳት ላይ ያላቸው አመለካከት እንዲጎለብት፣ እንዲሁም በንጹሕ አካባቢ የመማር መብት እንዳላቸውና አካባቢያቸውንም በንጽሕና መያዝ እንደሚገባቸው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየተሠራ ነው" ሲል አብራርቷል፡፡

እንደ ተማሪ ይስሐቅ ገለጻ፣ ክበቡ በየጊዜው በሚፈጥረው ግንዛቤ ተማሪዎች በጽዳትና በአረንጓዴ ልማት ላይ ያላቸው አመለካከት አድጓል፤ የግቢው ጽዳትም ተጠብቋል፡፡ ቀደም ሲል የፈተና ወረቀት ሲሰጣቸው ውጤቱን ካዩ በኋላ ቀድደው በመጣል ግቢውን በማቆሸሽ ገጽታውን ያበላሹ እንደነበርና አሁን ላይ ግን ይህን የሚያደርግ አለመኖሩ አንዱ ማሳያ ነው። ሌላው የክበቡ አባላት በግቢው ያሉ ፍራፍሬዎችን፣ አትክልቶችንና ዕፅዋትን ይተክላሉ፤ እንክብካቤም ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ግቢው አረንጓዴ ሆኗል፡፡ የአራዳ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ባለሙያዎችም ሥልጠናዎችን ይሰጣሉ። ለምሳሌ፡- ቆሻሻን እንዴት መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻልና በትንሽ ቦታ እንዴት የከተማ ግብርና መሥራት እንደሚቻል ያሠለጥናሉ፡፡

ከትምህርት ቤት ውጭ፤ በቤቱ የውኃ መያዣ ፕላስቲኮችን በመቆራረጥና ግድግዳ ላይ በመስቀል የጓሮ አትክልቶችን (ሰላጣና ቆስጣ...) በማልማት የቤተሰቡን የምግብ ፍጆታ በማሟላት እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከጓሮ አትክልቶች በተጨማሪም የተለያዩ የአበባ ዓይነቶችን ተክሎ እየተንከባከበ እንደሚገኝ ነው ተማሪ ይስሐቅ የገለጸልን፡፡

ተማሪ ሜሮን በነጋም በተመሳሳይ ከተፈጥሮ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ እንደሚያስደስታት፣ ወደ አካባቢ ጥበቃ ክበብ ከገባች አንድ ዓመት እንደሆናትና የክበቡ ጸሐፊ በመሆን እያገለገለች ትገኛለች፡፡ ክበቡ የግቢውን ጽዳት ከመጠበቅ ባለፈ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበብ ጋር በመሆን የማያገለግሉ ቁሳቁሶችን በመልሶ መጠቀም አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ እየሠራ ነው። እሷም አፈር እንዳይሸረሸር፣ ለአካባቢ ውበትና የአካባቢ ሙቀት እንዳይጨምር በመቆጣጠር ረገድ ዛፍ ካለው ጥቅም አንጻር ችግኞችን መትከል፣ እንዲለሙ እንክብካቤ ማድረግ እንዲሁም እንዳይቆረጡ መጠበቅ ላይ የድርሻዋን እየተወጣች እንደምትገኝ ገልጻለች፡፡

የተማሪ ሜሮን ቤተሰቦች ቲማቲም፣ ሰላጣ፣ ቆስጣና ድንች በማልማት ተጠቃሚ የመሆን ልምድ እንዳላቸውና እሷም በራሷ በትንሽ ቦታ የጓሮ አትክልቶችን እንዴት መትከልና ማልማት እንደሚቻል ግንዛቤዋ እያደገ መምጣቱን ትናገራለች፡፡ "ተማሪዎች አካባቢያችሁን ንጹሕ በማድረግና ዛፎችን የመትከል ባሕል በማዳበር አካባቢያችሁን ጠብቁ፤ ይህን ስታደርጉ በምላሹ ጥሩ ነገር ታገኛላችሁ" የሚል መልዕክት አስተላልፋለች፡፡

ተማሪ ዳግም አንሙት ደግሞ በክበቡ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ለአራት ዓመታት ያህል መሳተፉን ይናገራል። ክበቡ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ከመትከል ባሻገር አድገው ጥቅም ላይ እስኪውሉ ድረስ እንክብካቤ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡ አላስፈላጊ አረሞችን በማስወገድ መኮትኮት፣ ማረምና ውኃ የማጠጣት እንዲሁም ሚኒ ሚዲያውን በመጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እየሠራ ነው፡፡ በዚህም ግቢው ውብ እንዲሆንና ገጽታው እንዲለወጥ ተደርጓል፡፡ የክበቡ አባላት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበብ አባላት ጋር በመሆን በመልሶ መጠቀም ረገድ፤ ለምሳሌ፡- ከተቆራረጡ እንጨቶች ለሚኒ ሚዲያው አባላት ቆመው የሚናገሩበት መድረክ (አትሮኖስ) የማዘጋጀት ሥራ ሰርተናል ሲልም ይገልጻል፡፡

መምህር ማስረሻ ፍቃዱ የክበቡ ተጠሪ ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቱ ለ6 ዓመታት ያህል መቆየታቸውንና ክበቡን ለማጠናከር በየዓመቱ መስከረም ወር ከተማሪዎችና መምህራን በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የአባላት ምዝገባ እንዲካሄድ ማድረጋቸውን ይናገራሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ የአባላት ምዝገባ ከተካሄደ በኋላ የዓመት ዕቅድ በማዘጋጀት በአካባቢ ጥበቃ ላይ የተለያዩ ሥራዎች ይሠራሉ። በሳምንቱ መጨረሻ ዓርብ ሁሉም የሚሳተፍበት የግቢ ጽዳት ይካሄዳል፡፡ ክበቡ በግቢው የለሙ ዛፎች እና የጓሮ አትክልቶች እንክብካቤና ጥበቃ ያደርጋል። በዚህም ግቢውን አረንጓዴና ነፋሻማ ማድረግ ተችሏል፡፡ የክበቡ አባላት አገር በቀል ችግኞች እንዲተከሉና እንዲጸድቁ ውኃ በማጠጣትና በመኮትኮት የመሪነት ሚናቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪው እንዴት አካባቢውን መጠበቅ እንዳለበት በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው ንድፈ-ሐሳባዊ ትምህርት በተጨማሪ በሳምንት አንድ ቀን በሚኒ ሚዲያ ግንዛቤና ትምህርት ይሰጣል፡፡ በዚህም አሁን ላይ በትምህርት ቤቱ ግቢ የተተከሉት የፍራፍሬ ዛፎች ግቢውን ከማሳመር ባሻገር እንደ ማንጎና አቮካዶ ያሉት ምርትና ጥቅም እየሰጡ ይገኛሉ። በተጨማሪም በየዓመቱ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር እየተከናወነ ነው፡፡

በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የአካባቢ ጥበቃ ትምህርትና ግንዛቤ ቡድን መሪ አቶ አንበሳው ፈንታ እንደሚያስረዱት፣ የአካባቢ እንክብካቤ ክበባት የመቋቋማቸው ዓላማ ተማሪዎችና አዳጊ ሕፃናት ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለ አካባቢ ምንነት እንዲያውቁ፣ እንዲንከባከቡ፣ ተቆርቋሪና ተሟጋች ሆነው እንዲያድጉ፣ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግና የትምህርት ቤቱን ማኅበረሰብ በማነሳሳት ተሳትፎ እንዲያደርጉ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ነው፡፡

እንደ ቡድን መሪው አቶ አንበሳው ገለጻ፤ በአዲስ አበባ ከተማ በ2017 በጀት ዓመት 500 በሚሆኑ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአካባቢ እንክብካቤ ክበባትን መልሶ የማቋቋም ሥራ ተሠርቷል፡፡ በዘንድሮው በጀት ዓመት በግማሽ ዓመት 520 ክበባት የተቋቋሙ ሲሆን ይህም በ11ዱም ክፍለ ከተሞች አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መከፈታቸውንና በእነዚህም ተጨማሪ 20 ክበባት በመቋቋማቸው ነው፡፡

የአካባቢ እንክብካቤ ክበባት ለምን እንደሚቋቋሙና ምን ምን ሥራዎችን እንደሚሠሩ የማቋቋሚያ መመሪያ (ማንዋል) አላቸው፡፡ በመመሪያው(ማንዋሉ) መሠረትም ክበባቱ የራሳቸው ሰብሳቢና ጸሐፊ አላቸው፡፡ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል አንዱ በትምህርት ቤታቸው የተለያዩ አካባቢያዊ ጉዳዮችን መሥራት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ችግኞችን የመንከባከብ ሥራ ይሠራሉ፡፡ የትምህርት ቤቱን ማኅበረሰብ በማስተባበር የጽዳት ዘመቻ ያካሂዳሉ፡፡ ዕፅዋት እንዴት ተዘርተው እንደሚበቅሉ፣ በምን ያህል ጊዜ እንደሚያድጉ፣ ምን ዓይነት አፈር፣ ውኃና አየር እንደሚያስፈልጋቸው ለሌሎች ተማሪዎች ማስተማሪያ የሚሆኑ ሞዴል ፓርኮችን የማቋቋም ሥራ ይሠራሉ፡፡ የዓለም የብክለት መከላከል ቀን፣ የዓለም አካባቢ ቀንና የደን ቀን የሚባሉ በየዓመቱ የሚከበሩ የአካባቢ ቀናትን ያከብራሉ። በችግኝ ተከላ ላይ ለትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ግንዛቤ የመፍጠርና የማስተባበር ሥራ እንደሚያከናውኑም የቡድን መሪው ያብራራሉ፡፡

አቶ አንበሳው እንደገለጹት፣ አካባቢያቸውን ከድምፅ፣ ከፍሳሽ፣ ከአየር እና ከደረቅ ቆሻሻ ብክለቶች እንዲሁም ትምህርት ቤቱን የሚያውኩ የአካባቢ ብክለቶችን በመከላከል ረገድ ክበባቱ ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ፡፡ ክበባቱ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጡ ወይም የተቋቋሙለትን ዓላማ እንዲያሳኩ በየደረጃው ከሚገኙ የወረዳ አደረጃጀቶች ጋር በመነጋገር የድጋፍና ክትትል ሥራ ይሠራል፡፡ አንደኛው ስለ አካባቢ ምንነት ሥልጠና መስጠት ነው፡፡ በየክፍለ ከተማው ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉ አነስተኛ ፓርኮች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በፓርኩ ውስጥ የሚተከሉ ችግኞችን የማቅረብ፣ የውኃ ማጠጫዎችን፣ ለመቆፈሪያና መኮትኮቻነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን የማገዝ እንዲሁም በሚተከሉ ነገሮች ላይ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡ የክበባት የጉዞና የዘመቻ፣ የአካባቢ ብክለትን የመከላከልና የማስተማር ሥራዎችን በተመለከተ በቅርበት ያለው የክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ድጋፍ ያደርግላቸዋል፡፡

በክበባት መቋቋምና መጠናከር ምክንያት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትምህርት ቤቶች ንጹሕና አረንጓዴ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ በትምህርት ሥርዓቱ አካባቢያዊ ጉዳዮች መካተታቸው ተማሪዎች ስለ አካባቢያቸው ያላቸው ግንዛቤ እንዲያድግ እያደረገ እንደሚገኝ አቶ አንበሳው አክለው አስረድተዋል፡፡

# የተገልጋዮቹ ቅሬታና የተቋሙ ምላሽ

**“ከዚህ በፊት ቅሬታችንን አሰምተናል፤ ነገር ግን ዘላቂ መፍትሄ አልተሰጠንም”**

**በቦሌ አራብሳ ሰፈራ የሚኖሩ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት ተጠቃሚ ሰራተኞች**

**“ችግሩን ለመፍታት እየሰራሁ ነው”**

**የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት**

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
የመንግስት ሰራተኞች በፐብሊክ ትራንስፖርት ሲገለገሉ

ወይዘሮ አየለች ጎዳ ቦሌ አራብሳ ሰፈራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሳይት አምስት ነዋሪ ናቸው፡፡ ጠዋት ከቦሌ አራብሳ ወደ ፒያሳ ማታ ደግሞ ከፒያሳ ቦሌ አራብሳ መጓጓዝ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ነው። በየእለቱ እንዲመላለሱ ያስገደዳቸው ህይወታቸውን የሚመሩበት ስራቸው ሲሆን የሚመላለሱትም ለመንግስት ሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ በተመደቡት አውቶብሶች ነው፡፡ “ይህ መሆኑ እኔን ጨምሮ የመንግስት ሰራተኛው በሰዓቱ ስራ ቦታ ደርሶ በአግባቡ እንዲያገለግል ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ ታክሲ ጋር በመሰለፍ የሚያጠፋውን ጊዜና ገንዘብም ታድጎለታል” ሲሉ ፋይዳውን ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ አየለች አገልግሎቱ እጥረት እንዳለበት አልሸሸጉም፡፡ “ወንበር ሳይሆን መቆሚያ ቦታ ለማግኘት ከቤቴ 11፡00 ሰዓት እወጣለሁ፡፡ ለ2፡00 ሰዓት ያህልም እቆማለሁ፡፡ በዚህ ምክንያት ወገቤን እና እግሬን ያመኛል፡፡ በስራ ቦታም በጠዋት ስለሚደክመኝ ስራዬን ደስተኛ ሆኜ ለመስራት እቸገራለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የስራ ባልደረቦቼ በሌሊት ሲወጡ የድብደባ ወንጀል ደርሶባቸው ተመልክቻለሁ” ሲሉም አብራርተዋል፡፡

“የጠዋት መቆሜ ማታም እንዳይደገም ከስራ ሰዓት ቀደም ብዬ እወጣለሁ” የሚሉት ወይዘሮ አየለች፣ ለጉዳዩ ዘላቂ መፍትሄ ሊሰጠው እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

በዚህ መስመር ስላለው የመንግስት ሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ሀሳባቸውን ያጋሩን ሌላኛው አስተያየት ሰጪ በተገልጋዮቹ ተመርጠው የማስተባበር ስራ እየሰሩ የሚገኙት ኮሎኔል ደምሴ ተሰማ ናቸው። በአስተያየታቸውም፣ “የምንሳፈርበት አውቶቡስ ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት በሚሰለፉ ተገልጋዮች ይሞላል፡፡ እነዚህ አካላት ሌሊት ወጥተን እንነሳም በሚሉበት ወቅት ህፃናት የያዙ፣ ነፍሰጡር እናቶች እና አቅመ ደካሞችም ጭምር ወንበር እንዲያገኙ ለማድረግ ያለው ፈተና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ተገልጋዩ ረጅም ሰዓት ከመቆሙ የተነሳ ለጤናም ችግር እየሆነበት ነው፡፡ ይህ ችግር ይፈታልን ዘንድ ከዚህ በፊት ቅሬታችንን አሰምተናል፣ ነገር ግን ዘላቂ መፍትሄ አልተሰጠንም” ብለዋል፡፡

“ነፍሰጡር ሆኜ፣ ህፃን ይዤ ወይም አቅመ ደካማ ሆኜ ስለማያዩኝ ሰዎች አይረዱኝም፡፡ የውስጤን ህመም እኔና ፈጣሪ ብቻ ነን የምናውቀው፡፡ አንዱ ኩላሊቴ ፌል አድርጎ ቀሪው አንዱም ግማሽ ክፍሉ ተጎድቷል ተብዬ በግማሽ ኩላሊት ነው የምኖረው፡፡ በዚሁ ላይ መቆም ሲጨመርበት ምን ያህል ሊያባብሰው እንደሚችል መገመት አያዳግትም” የሚሉት ደግሞ ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ስማቸው ለዚህ ፅሁፍ ሲባል የተቀየረ ወይዘሮ ሰላም አንዳርጌ ናቸው፡፡

“ይህንን ችግሬን ተረድቼ መነሻውን ቦሌ አራብሳ አድርጎ እስከ ፒያሳ የሚወስደውን አውቶቡስ ለመያዝ 11፡00 ሰዓት ከቤቴ እወጣለሁ፡፡ እንደዚህም ሆኖ ወንበር የማላገኝባቸው ቀናት ብዙ ናቸው፡፡ ህፃናቱም አየር ሲያጥራቸው ያለቅሳሉ” የሚሉት ወይዘሮዋ፣ ይህ የሆነው በቂ አውቶቡስ ባለመኖሩ ምክንያት እንደሆነና የሚመለከተው አካል ለጉዳዩ ተገቢው ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቀዋል፡፡

የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል በዚህ መስመር ከወራት በፊት በሰራው ዘገባ መሰል ችግሮች እንደነበሩ መዘገቡ ይታወሳል፡፡ ስለዚህ በዚህ ልክ እየተነሳ ላለው ጉዳይ እና በሌሎች ረጅም ርቀት ባለባቸው አካባቢዎች ያለውን መሰል ችግር ለመፍታት ምን እየተሰራ እንደሆነ መልስና ማብራሪያ እንዲሰጡን በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሪት ቤዛዊት ተሾመን ጠይቋል፡፡

**ሰዎች በብዛት የሚኖሩባቸውን ቦታዎች ያማከለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማቅረብ በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የሙሉ መስመሮች መረጃ በጂ አይ ኤስ ተይዞ ጥናት እየተደረገበት ይገኛል**

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ገለጻ፣ የመንግስት ሰራተኛው በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት አገልግሎት የሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት ከተጀመረ 11 ዓመት ሆኖታል፡፡ ይህም ሰራተኛው በሰዓቱ ተገኝቶ ስራውን በአግባቡ እንዲሰራ በማድረጉ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ ከማድረግ እና እጥረቱን ከመቅረፍ አንፃር አሁንም የሚነሱ ቅሬታዎች እንዳሉ ያልሸሸጉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፣ የመንግስት ሠራተኛው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሥራና የመኖሪያ ቦታ ይቀያይራል። ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሰራተኛ በማስፋፊያ አካባቢዎች ይኖራል። ይህንን ችግር በጊዜያዊነት ለመፍታት መስመሮችን የመጨመር እንዲሁም የማራዘም ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ይህም ማለት የሰው ብዛቱ አነስ ያለባቸው ቦታዎች ላይ ሁለት አውቶቡሶች ካሉ አንዱን ብቻ እንዲጠቀሙ በማድረግና አንዱን ደግሞ እጥረት ባለባቸው ቦታዎች አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በዚህም ለምሳሌ፡- ኮዬ ፈቼ ከ20 አውቶቡሶች ወደ 35 ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

ሌላኛው በጊዜያዊነት እንደመፍትሄ የተወሰደው 17 የሚሆኑ ሃገር አቋራጭ አውቶቡሶች ለሰራተኛው አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ስራ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በየቅርንጫፉ ተጠባባቂ ተብለው የሚቀመጡ ከሁለት እስከ አራት አውቶብሶችም ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉንም አብራርተዋል፡፡

ሰዎች በብዛት የሚኖሩበትን ቦታ ያማከለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማቅረብ በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የሙሉ መስመሮች መረጃ በጂ አይ ኤስ ተይዞ ጥናት እየተደረገበት ይገኛል፡፡

“ሌላኛው በፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያለውን እጥረት በቋሚነት የሚፈታው አውቶቡሶችን ገዝቶ ማስገባት ነው፡፡ ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ከዚህ በፊት 90 ፐብሊክ ሰርቪሶችን ለመግዛት ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ 2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በሚወስድ ገንዘብ ግዢ ለመፈጸም ውል መገባቱ ይታወሳል፡፡” የሚሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፣ ነገር ግን ከባንክ ብድር ማግኘት ስላልተቻለ ግዥው ሳይፈፀም መቆየቱንና በአሁኑ ወቅት ሌሎች የፕሮጀክት ስራዎችን በማቆም የአውቶቡስ ግዥው እንዲካሄድ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

መኪናዎቹ ብዙ ዓመት አገልግሎት ከመስጠታቸው ጋር ተያይዞ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን በማስጠገን ቶሎ ወደ ስራ እንዲገቡም እየተደረገ ይገኛል። እንዲህም ተደርጎ አሁንም ድረስ ቅሬታዎች እየቀረቡ መሆኑን እና ተቋሙ መፍትሔ ለመስጠት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ተናግረዋል፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 3 የዞረ

በአሁኑ ወቅት ወጣቶች በምሽት ቤተ-መጻሕፍት ገብተው ሲያነቡ ማየት ትልቅ ብሔራዊ ተስፋ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የሳይንስ ሙዚየም በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ግምት የሚሰጠውና በሳይንስ የበለፀጉ ሀገራት መሪዎች ሳይቀሩ አድናቆታቸውን የገለጹበት ስራ መሆኑን አንስተዋል።

በሌላ በኩል፣ ኢትዮጵያ ያላትን ታላቅ ታሪክ የሚመጥንና ብሔራዊ ኩራትን የሚያጎለብቱ እንደ ዓድዋ ድል መታሰቢያና የቤተ-መንግስት ሙዚየሞች ያላቸውን ስልታዊ ጠቀሜታ አብራርተዋል።

ለአብነትም ከዚህ ቀደም ለውጭ ሀገር የክብር እንግዶች አበባ የሚቀመጥበትና የሀገርን ታሪክ የሚናገር ስፍራ አለመኖሩ ለኢትዮጵያ አሳፋሪ እንደነበር ያስታወሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አሁን የተገነቡት የዓድዋ ሙዚየሞች ገንቢ ሀገራዊ ትርክት በማስረፅ ዜጎች በማንነታቸው እንዲኮሩና የአርበኝነት ስሜታቸው እንዲጎለብት እንደሚያደርግም ጠቅሰዋል::

አዲስ አበባ እንደ ኒው ዮርክ፣ ፓሪስ እና ሪዮ ዲጄኔሮ ከተሞች የራሷ የሆኑ ዓለም አቀፍ መለያዎች (Landmarks) ሊኖሯት እንደሚገባ የተናገሩት ጠቅላ ሚኒስትሩ በተለይ በእንጦጦ እና በየካ አካባቢ የተሰሩ ስራዎች ከተማዋን እንደ ‘ሆሊውድ’ ያሉ ዓለም አቀፍ የቱሪስት መስህቦች ባለቤት እንደሚያደርጓት አመላክተዋል።

እነዚህ የልማት ስራዎች የቱሪስት መስህብ ከመሆን ባለፈ፣ አዲሱ ትውልድ የሀገሩን ማንነት አውቆ በኢትዮጵያዊነቱ እንዲኮራና የአርበኝነት ስሜቱ እንዲገነባ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ይህ ከተማን ዘመናዊ የማድረግ ስራ የኢትዮጵያን የክብር ታሪክ ለዓለም በሚመጥን መልኩ ለማሳየት ያለመ መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል።

አዲስም አበባም፤ የሆነችው አዲስ አበባ፣ ዘመኑን በዋጁ እና ጎስቋላነታቸውን በነበር እተኩ ባሉ ወንዞቿ፣ በሙዚየሞቿ፣ በመናፈሳቿ፣ በውብ ጎዳናዎቿ... የውበትን ሸማ ተጎናፅፋ አላፊ አግዳሚውን ከራሱ፣ ከተፈጥሮ እና ከዘመን ጋር እያስታረቀች መሆኑንም በርካቶች በመመስከር ላይ ናቸው::

## ለምርጫው ... ከገጽ 6 የዞረ

ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በወጣቶች አማካኝነት ይታደላል። ባለፈው ዓመት በነበረው የኢድ በዓል እስከ 20 ኩንታል ዱቄት ተሰባስቦ ድጋፍ ፈላጊ ለሆኑ ዜጎች እንዲሰራጭ በማድረግ በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፉ ተደርጓል:: በዘንድሮ በዓልም ይህ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በኢድ አልፈጥር በዓል የሚደረገው የመደጋገፍ እሴት በእለት ተለት ህይወት ሊተገበር እንደሚገባ ሼህ አሊ ይናገራሉ። “ዘካ መስጠት ግዴታ ነው:: የሰዎችን ማህበራዊ ችግር ያቃልላል:: የነብዩ መሐመድ መርህንም መከተል ነው:: የእርሳቸው መርህ አንዱ ለአንዱ ማዘን ነው:: ለሰው የማያዝን ከእኔ አይደለም፤ አላህ አያዝንለትም” ብለዋል:: ይህንንም ህዝበ ሙስሊሙ እንዲተገብረው ማታ ከሶላት በፊት በየመስጂዱ ትምህርት ይሰጣል::

አቅም የሚያንሳቸው፣ በችግር ምክንያት ደስታ የራቀቸው ሰዎች፣ ራሳችን ደስታ እንዳገኘን ሌሎችም ደስ እንዲላቸው ትንሽና ትልቅ ሳይል የዘካ ግዴታውን መወጣት ይኖርብናል:: ነብዩ መሐመድ ‘በአንተ ቤት ደስታ ኖሮ በጎረቤትህ ከሌለ፤ በቤትህ እየበላህ፤ ጎረቤትህ የሚራብ ከሆነ አንተ ከእኔ አይደለህም፤ ነገ በአላህ ዘንድ ያስቀጣል” እንዳሉት በተግባር መገለጥ እንዳለበት ምክራቸውን ለግሰዋል::

በጥቅሉ ዘካ ከራስ በፊት ለሌላው ማሰብን የሚያስተምር ሥርዓት ነው። እንዲህ ዓይነት እሴቶች አካል ጉዳተኞችን፣ ድኾችን፣ ዐቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ሕጻናትንና የተለያዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ማህበራዊ ችግሮች በማቃለል ትስስርን፣ መደጋገፍንና መተባበርን የሚያጠናክር በመሆኑ ትውልዱን በማስተማር አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል::

ነት እንዲጎለብት ያግዛል:: የሚያቀርቡት ሐሳብም ለሀገር ሰላም፣ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና ለህገ መንግስታዊ ስርዓት መጠናከር የሚያግዝ መሆን ይገባዋል:: የዴሞክራሲያዊ ስርዓት እሴቶችን፣ የህግ የበላይነትን፣ መራጮች መብትና ኃላፊነታቸውን እንዲያውቁ፣ ሰላማዊ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲኖር መስራት ይኖርባቸዋል። ይህም በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንዲጠናከር ያደርጋል። የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ልማዶችም በህዝብ ዘንድ ግንዛቤና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያስችላል::

“ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በአንድ ጀምበር የሚገነባ አይደለም፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሀገር ቀርቶ ጠንካራ ተቋማት የገነቡና የዳበረ ዴሞክራሲ አላቸው በሚባሉ ሀገራት ሳይቀር ምንም ዓይነት እንከን የሌለበት ምርጫ ማካሄድ ያስቸግራል” የሚሉት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር)፤ ምርጫ ሂደት እንደመሆኑ ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ እንዲሄድ መስራትና ይህንንም ለህዝብ ማስገንዘብ ከምሁራን ይጠበቃል።

ምሁራኑ በምርጫው ሂደት የሚኖራቸውን ሚና ለመወጣት በፖለቲካው ውስጥ የሚታዩ ተግዳሮቶችን መጋፈጥ እንደሚጠበቅባቸው መኮንን (ዶ/ር) ያነሳሉ:: ለምሳሌ፡- በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋልታ ረገጥ ወይም ጽንፍና ጽንፍ የሆነ አቋም ሲያራምዱ ይታያል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ ርዕዮተ ዓለምና ፕሮግራም ቢኖራቸውም የመጨረሻ ግባቸው ሀገርን የሚያሻግር ሀሳብ ማቅረብ ላይ መሆን አለበት:: ከዚህ አንጻር ጽንፍና ጽንፍ የቆመ ሀሳብ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲቀራረቡና ወደ መሀከል እንዲመጡ በማለዘብ ረገድ ምሁራን ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል:: ገዥው ፓርቲ ወይም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ‘እንዲህ ናቸው፤ እድል አይሰጡም’ በማለት ራስህን ማግለል ሳይሆን ችግርም ካለ ለመጋፈጥ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል::

በዘርና ማንነት በመታጠር፤ ለራሳቸው ጎሳና ማንነት ወይም አካባቢ ብቻ በማድላት መስራት የለባቸውም:: ሀገራዊ እይታን ማዕከል አድርገው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል:: ለሀገር ግንባታ፣ ለሰላማዊ የስልጣን ሽግግር፣ የተሳካ ምርጫ ለማካሄድ የሚጠቅም ሐሳብ እስካላቸው ድረስ ሐሳባቸውን በመገናኛ ብዙሃን ለማካፈል ወደኋላ ማለት የለባቸውም፤ ገፍተው በመሄድ መሳተፍ እንዳለባቸውም የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ መኮንን (ዶ/ር) ያስገነዝባሉ::

በአራዳ ክፍለ ከተማ አምስት ኪሎ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ዮሐንስ አሰፋ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የመራጭነት ካርድ ቀድመው በማውጣት፤ የፖለቲካ ፓርቲ የክርክር መድረኮችን በመከታተል ይሆነኛል ለሚሉት የፖለቲካ ፓርቲ ድምፃቸውን ለመስጠት እየተጠባበቁ ይገኛሉ:: ምርጫው ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ከተፈለገ ሁሉም ዜጋ የምርጫን ዓላማ በደንብ መገንዘብ ይኖርበታል::

በምርጫው የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገር ይጠቅማል የሚሉትን ሐሳብ ይዘው ይቀርባሉ:: ከዚህ ውስጥ በትክክል ኅብረተሰቡን ሊጠቅም የሚችለው ሀሳብ የትኛው ነው የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል:: በዚህ ላይ ምሁራን ኅብረተሰቡን ማስተማር መቻል አለባቸው::

ከምርጫው ሂደት አንስቶ የሚከናወኑ ሥራዎችን በመከታተልና ክፍተቶች ሲመለከቱም እንዲስተካከሉ በማድረግ መሳተፍ ይኖርባቸዋል:: ኅብረተሰቡ ከምንም በላይ በሰላማዊ መንገድ፣ በሐሳብ የበላይነት ችግሮችን መፍታት እንደሚቻልና ለዚህም በመምረጥ የዜግነት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማስተማር እንደሚጠበቅባቸው ይናገራሉ::

በመጪው አምስት ዓመታት ይመራኛል ብሎ ለሚያምነው የፖለቲካ ፓርቲ ውክልና ለመስጠት የመራጭነት ካርድ በማውጣት የድምፅ መስጫ ዕለቱን እየተጠባበቀ እንደሚገኝ የሚናገረው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ነዋሪው ወጣት አክመል አህመድ፣ ምርጫው ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሆኖ እንዲካሄድ ምሁራን ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው ይላል:: ምሁራን የተሻለ እውቀትና ሐሳብ ያላቸው እንደመሆኑ ለከተማና ለሀገር ይበጃል ተብሎ የሚታሰበውን አካል ኅብረተሰቡ ለይቶ እንዲመርጥ በማንቃት፣ አቅጣጫ በማሳየትና በማስተማር መሥራት እንደሚገባቸው ተናግሯል::

## የ“ባለጉዳይ” ... ከገጽ 8 የዞረ

በአካል ብሎም በፅሑፍ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አመራሩ ብቻ ሳይሆን ታች ድረስ ያለ ባለሙያ ጭምር አጥጋቢ ምላሽ እየሠጠ ይገኛል:: ይህን አይነቱን ግንዛቤ በባለሙያዎች ዘንድ እንዲፈጠር ከማድረግ አንጻር የተለያዩ የግንኙነት መድረኮች ላይ በግልፅ በመነጋገር መፍትሄ ላይ ስለመደረሱ ገልፀዋል። ባለሙያዎች ብሎም አመራሮች ከስራ ሰዓት ውጪ መሥራትን ባህል አድርገው እያገለገሉ ይገኛሉ:: ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት ለሚነሱ ቅሬታዎች ከስር ከስር መፍትሄ እየሰጡ የመሄድ ባህልን እያዳበርን እንገኛለንም ብለዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የአገልግሎት አሰጣጥ አውትሶርስ ኃላፊ አቶ በቀለ ተመስገን ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ ከተማ አስተዳደሩ ረቡዕና አርብ የባለጉዳይ ቀን በሚል አመራሩ በቢሮው ተገኝቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲወሰን የራሱ የሆነ ዓላማ አለው:: በቀጥታ ማኅበረሰቡ አመራሩን አግኝቶ ጉዳዩን እንዲያስረዳ እድል የሚፈጠርበት ነው ብለዋል::

እንደ አቶ በቀለ ገለፃ፤ ተገልጋዩ ማኅበረሰብ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች በቀጥታ የሚመለከተው አመራር ሌላ ሶስተኛ ወገን ሳያስፈልግ ውሳኔ ሰጪውን አካል እና የተቋሙን ኃላፊዎች በቀጥታ አግኝቶ ቅሬታቸውን ማቅረብ እና መፍትሄ ማግኘት እንዲችሉ ማስቻል ነው:: ያቀረቡትን ጥያቄ ደግሞ አመራሩ አዳምጦ በመረዳት የታዩ የብልሹ አሰራርና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን እንዲፈታ አቅጣጫ ተቀምጧል::

አቶ በቀለ እንደተናገሩት፣ በ2016 ዓ.ም የባለጉዳይ ቀንን ተግባራዊነትና አፈፃፀሙን በተመለከተ ቅኝት ተደርጎ ነበር:: በዚህም ገና ልምምዱ አዲስ ስለነበር 63 ነጥብ 5 በመቶ የሚሆነው አመራር ብቻ ነበር ቢሮ ላይ ቁጭ ብሎ ባለጉዳይን ሲያስተናግድ የነበረው:: የተቋም ኃላፊዎችን ሰብስበን ማስተካከያ እንዲደረግ ተደርጓል:: በዚህም ከዓመት ዓመት እንዲሁም በየሩብ ዓመቱ መሻሻሎችን ለማየት ተችሏል:: በ2018 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት አፈጻፀምን በተመለከተ 94 በመቶ የሚሆኑት ተሿሚ አመራሮች በባለጉዳይ ቀን ቁጭ ብለው አገልግለዋል:: በተለያየ ሙያ የሚያገለገሉ ባለሙያዎች በተዋረድ 90 በመቶ የሚሆኑት ለተገልጋይ አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት መቻላቸውን ቢሮው ያደረገው የምልከታ ግኝት እንዳመላከተ አስቀምጠዋል::

እንደ አቶ በቀለ ማብራሪያ፤ ቢሮ ተቀምጦ አገልግሎት ሰጠ አልሰጠ ብቻ የሚለው ነገር ብቻ በቂ አይደለም:: “ህዝብን በምን አግባብ እያገለገለ ነው” የሚለውን ለመቃኘት ከተገልጋይ ጭምር እርካታ እየተሰበሰበ ይገኛል:: በተለይም የመማክርት ጉባኤ የተገልጋይ ካውንስል በሁሉም ተቋማት ላይ የተደራጀበት አግባብ አለ:: በዚህም አገልጋዩ ከተገልጋዩ ጋር ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተት በማጥበብ ረገድ እገዛ እያደረገ መሆኑን ገልፀዋል::

እንደ አቶ በቀለ ገለፃ፤ እስካሁን በተሠራው ሥራ የተገኘው ውጤት የአገልግሎት አሰጣጡ በከተማ አቀፍ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥሩ እመርታዊ ለውጥ እያስመዘገበ ይገኛል:: የክትትልና ድጋፍ አግባቦችን ካለመቆራረጥ የማድረግ እንዲሁም ተጠያቂነትን የማስፈን ሥራ እየተሠራ ይገኛል:: በተሠራው ሥራም መብቱን በአግባቡ የሚያውቅ ማኅበረሰብ እየተፈጠረ ነው:: በተለይም በአንድ ማዕከል አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ አካላት አመራሩ ፊት ለፊት በመገኘት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ መደረጉ ባለጉዳዩ አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኝ ያግዘዋል:: ከዚህ በተጨማሪም አመራሩ ለተነሱ ጥያቄዎች በቶሎ ምላሽ የመስጠት ባህሉን ማዳበር በመቻሉ ምክንያት ባለጉዳዮች እንዳይንገላቱ ብሎም ጊዜና ጉልበታቸውን እንዲቆጥቡ ያስችላቸዋል። ትክክለኛነት አልያም አግባብነት የሌለውን ጥያቄ ባለጉዳዩ በሚያነሳበት ወቅትም እዚያው የሚታረምበት አግባብ በመኖሩ ምክንያት የአመራሩንም የባለጉዳዩንም ጊዜ መቆጠብ ተችሏል::

ከተገልጋዩ ማህበረሰብ ጉቦ አልያም እጅ መንሻ መቀበል ብቻ ሳይሆን፤ በተገቢው መንገድ ተገልጋዩን ማህበረሰብ አለማገልገል በራሱ ያስጠይቃል። የትኛውም አመራርም ሆነ ባለሙያ ተገልጋይን የሚያመናጭቅ ከሆነ ተጠያቂ ከመሆን አይድንም:: በከተማ አቀፍ ደረጃ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በተደረገው የአፈፃፀም ግምገማ መሠረት ቁጥራቸው 3 ሺህ 842 የሚሆኑ ከአመራሮች እስከ ታችኛው ባለሙያ ድረስ የሚገኙ አካላትን ተጠያቂ ለማድረግ ተችሏል:: አገልግሎትን በተገቢ አግባብ መፈፀም ያልቻሉ ቁጥራቸው ወደ 61 የሚጠጉ ተሿሚ አመራሮች፣ በዳይሬክተርና ቡድን መሪ ደረጃ 126 እንዲሁም ቁጥራቸው ወደ 3 ሺህ 542 ባለሙያዎች ተጠያቂ ስለመደረጋቸውም ኃላፊው አስታውቀዋል::

# የስራ ቅጥር ማስታወቂያ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሐብት ልማት ጽ/ቤት በወረዳ አስተዳደሩ ጽ/ቤቶች ውስጥ ባሉ ክፍት ስራ መደቦች ላይ ሰራተኞች ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የስራ መደብ መጠሪያ | የስራ ደረጃ | ደሞዝ | ብዛት | ተፈላጊ ችሎታ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የስራ ሁኔታ | የስራ መደቡ የሚጠይቀው የት/ደረጃ | የስራ መደቡ የሚጠይቀው የስራ ልምድ | የስራ መደቡ የሚገኝበት ጽ/ቤት |
| 1. | የጽዳትና ተላላኪ ሰራተኛ | II | 6,365.00 ደሞዝና በተጨማሪም 1500.00 የቤት ኪራይ አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች | 3 | በቋሚነት | 8ተኛ፣ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | 4/3/2 | አ/ከ/ክ/ከ/ወ/8/ አስተዳደር |
| 2. | የማህበራዊ ፍ/ቤት ሬጅስተራር | VII | 8478.00 ደሞዝና በተጨማሪም 1500.00 ብር የቤት ኪራይ አበል | 1 | 2 ዓመት | በህግ | ዲፕሎማ ሌቭል 3፣ 4 | አ/ከ/ክ/ከ/ወ/8/ አስተዳደር በማህበራዊ ፍ/ቤት |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ተመዝጋቢዎች ኦርጅናል ትምህርትና ስራ ልምድ ማስረጃ እና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪነት መታወቂያ ያለው የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ከግል መስሪያ ቤት የተገኘ ስራ ልምድ የስራ ግብር ስለመከፈሉ የሚገልጽ ከግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የምዝገባ ቦታ፡- አዲስ አበባ አቶቢስ ተራ 500 ሜትር ዝቅ ብሎ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት 3ኛ ፎቅ ፐብሊክና ሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳደር ቡድን፡፡
4. የምዝገባ ጊዜ፡- ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉ 5 ተከታታይ የስራ ቀናቶች ይሆናል፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡-** 0118-2997-34

## አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 ፋይናንስ ጽ/ቤት

---

**የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር**

## የኦዲት ሥራ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር ማኅበሩን የ2017/2018 ዓ.ም የሂሳብ ሥራ በህጋዊ ኦዲተር አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

ተወዳዳሪዎች ለመመዝገብ የሚከተለውን ማስረጃ ይዘው በኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር ቢሮ መስቀል አደባባይ የድሮው አድማስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሕንፃ 1ኛ ፎቅ በአካል በመገኘት መመዝገብ ይችላሉ፡፡ ተወዳዳሪዎች ለመመዝገብ የሚከተሉትን ዶክመንቶች ማቅረብ አለባቸው ፡-

1. የታደሰ የ2018 ዓ.ም የንግድ ፈቃድ
2. የድርጅቱ TIN ቁጥር ሰርተፊኬት
3. የብቃት ማረጋገጫ ፎቶ ኮፒ
4. የግብር መክፈያ ሰርተፊኬት ማቅረብ አለበት፡፡

ማስታወቂያው ሥራ ላይ የሚቆይበት ግዜ ለሕትመት ከበቃበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ  አምስት የስራ ቀናት ብቻ ይሆናል።

**ለበለጠ መረጃ**

ስልክ፡-+251922654949/+251911063461 ላይ ይደውሉ

**የኢትዮጵያ ነጋዴ ሴቶች ማህበር**

---

አይሻ ሙሰማ ሹሁራላ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ አ/ቃ/10/4/13/125968/00 የሴሪ ቁጥር 1639293 የይዞታ ስፋት 41.96 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወመ10/21275/18 በቀን 16/07/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፕሮጀክት 11 በህንፃ ቁጥር ቢ-07 በቤት ቁ ቢ-07/05 ካርታ ቁጥር አቃ/ከ/2/25/434/00 በሴሪ ቁጥር 1462682 አቶ ሰለሞን ካሳ ገበየሁ የተመዘገበ የኮንዶሚኒየም ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ  ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ካለ በማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ እንድታሳውቁን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በአዲስ ከተማ  ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 280 በወ/ሮ ገነት ገዳ አይጉት ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020900432 ሴሪ ቁጥር L 038247 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 08/07/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በገረመው መንግስቱ መንገሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 15 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር 01/75/22951/00 በሴሪ ቁጥሩ 015501 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር 029802 በሴሪ ቁጥር 013983 በወ/ሮ ውብነሽ ሀብቴ ወልዴ የተመዘገበ ይዞታ  ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት  የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ  ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ አስረስ ከበደ ደባልቄ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/9/87/1/3/11555/1245/01 ሴሪ ቁጥር 1620473 የቤት ቁጥር NRE/NG/1105 የሆነው ሰርተፍኬት ተመዝግቦ የሚገኘውን በቤት ባለቤትነት ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ መሀመድ ሳላህ ኡስማን ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር 02/71/5287/00 ሴሪ ቁጥር 059778 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የዋሊያዎቹ ተጠባቂ ፍልሚያዎች

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያና የአፍሪካ ዋንጫ ታሪክ ጥልቅ ቁርኝት አላቸው፤ እ.ኤ.አ በ1957 አህጉራዊው የእግር ኳስ ማህበር ሲመሰረትም ሆነ የመጀመሪያው ፉክክር ሲጀመር፣ የኢትዮጵያ ስም በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነበር። በ1962 የድል አክሊል በመድፋት የአህጉሪቱ የእግር ኳስ ንግሥት የነበረችው ኢትዮጵያ፣ ባለፉት አሥርተ ዓመታት ግን በታሪኳ የማይመጥን ረጅም የውጤት ማጣት ውስጥ ቆይታለች።

በደቡብ አፍሪካውና በካሜሩኑ የአፍሪካ ዋንጫዎች ላይ ብቅ ብሎ የነበረው ተስፋም ብዙም ሳይዘልቅ ተዳፍኗል። በተለይም ደቡብ አፍሪካ ባዘጋጀችው የ2013ቱ የአፍሪካ ዋንጫ፣ ዋሊያዎቹ ከ31 ዓመታት በኋላ ወደ አህጉራዊው መድረክ ሲመለሱ ያሳዩት ወጥ የሆነ የኳስ ቁጥጥርና ማራኪ የጨዋታ ስልት በመላው አፍሪካ አድናቆትን አትርፎ ነበር። በተለይም በወቅቱ ሻምፒዮን ከነበረችው ናይጄሪያ ጋር እስከ መጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ድረስ የነበረው ብርቱ ፉክክርና ከዛምቢያ ጋር የአቻ ውጤት የተጠናቀቀው ጨዋታ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ጭላንጭል ተስፋ ያሳየ አጋጣሚ ሆኖ ተመዝግቧል።

በተመሳሳይ በ2021 የካሜሩን ቆይታ ምንም እንኳን ቡድኑ ከምድቡ ማለፍ ባይችልም፣ ወጣትና ተስፋ ሰጪ ተጫዋቾችን ይዞ በታላላቅ ኮከቦች ፊት ያሳየው ድፍረት የተሞላበት እንቅስቃሴ ለወደፊቱ ትልቅ ትምህርት ጥሎ አልፏል። እነዚህ ሁለት ተሳትፎዎች ኢትዮጵያ በሜዳ ላይ ያሳየችው የቴክኒክ ብቃትና የተጫዋቾቿ መናበብ፣ በትክክለኛ ዝግጅትና በስነ-ልቦና ጥንካሬ የታጀበ ከሆነ አሁንም ከአህጉሪቱ ውጤታማ ብሔራዊ ቡድኖች መካከል መሰለፍ እንደምትችል ትልቅ ማሳያ ናቸው።

አሁን ዳግም በምስራቅ አፍሪካ በሚስተናገደው የ2027 አፍሪካ ዋንጫ ውድድር ላይ ደምቆ ለመታየት አዲስ የዝግጅት ምዕራፍ ከፍቷል። በኬንያ፣ ዩጋንዳ እና ታንዛኒያ በጋራ አዘጋጅነት ለሚካሄደው ይህ የአፍሪካ ዋንጫ ቅድመ ማጣሪያ ጉዞ ተጀምሯል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋሊያዎቹ) በዚህ የመጀመሪያ ምዕራፍ ከደሴቲቱ ሀገር ሳኦ ቶሜ እና ፕሪንሲፔ ጋር እንዲገናኙ ተደልድለዋል። ይህ የሁለት ግጥሚያዎች ፍልሚያ ዋሊያዎቹን ወደ ዋናው የምድብ ማጣሪያ ለማሸጋገር ወሳኝ ሲሆን፣ የመጀመሪያውን ጨዋታ በትናንትናው ዕለት ያካሄደ ሲሆን፣ የመልሱ ጨዋታ ደግሞ በቅርቡ ካፍ ባጸደቀውና በታደሰው የድሬዳዋ ስታዲየም መጋቢት 22 ቀን 2018 ዓ.ም እንደሚካሄድ ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ በ2027 የአፍሪካ ዋንጫ (AFCON) ቅድመ ማጣሪያ ላይ ከሳኦ ቶሜ እና ፕሪንሲፔ ጋር መደልደሏ ወደ ዋናው የምድብ ማጣሪያ ለማለፍ ወርቃማ ዕድል እንዳላት ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል። ሳኦ ቶሜ እና ፕሪንሲፔ በአፍሪካ እግር ኳስ ውስጥ አዳጊ ከሚባሉ ሀገራት ተርታ ትመደባለች። እስከ ዛሬ ድረስ በአፍሪካ ዋንጫ የመጨረሻው ውድድር ላይ አንድም ጊዜ ተሳትፋ አታውቅም። የካፍ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሳኦ ቶሜ እና ፕሪንሲፔ በፊፋ የደረጃ ሰንጠረዥ 188ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሲሆን፣ ዋሊያዎቹ ደግሞ በ145ኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።



ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በ2027 የአፍሪካ ዋንጫ ቅድመ ማጣርያ ጨዋታ ከሳኦ ቶሜ እና ፕሪንሲፔ ጋር ያደርጋል

> **ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳው ሲጫወት ያለው የማሸነፍ ዕድል ከሜዳ ውጭ ካለው ጨዋታ በ65 በመቶ ብልጫ አለው**

ይህ የ43 ደረጃዎች ልዩነት ለኢትዮጵያ አንጻራዊ ብልጫን የሚሰጥ ሲሆን፣ ሳኦ ቶሜ ባለፉት 10 ዓመታት ካደረገቻቸው የማጣሪያ ጨዋታዎች ውስጥ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑትን በሽንፈት አጠናቃለች፡፡ እንደዚሁም በ2023 ማጣሪያ ላይ ብቻ 22 ጎሎች የተቆጠሩባት መሆኑ፣ ለኢትዮጵያ አጥቂዎች ሰፊ የጎል ዕድል እንደሚኖር ማሳያ ነው። በ2023 ማጣሪያ ላይ በናይጄሪያ 10 ለ 0 በሆነ ሰፊ ውጤት መሸነፏ የሚታወስ ሲሆን፣ ይህም በመከላከያ መስመር ላይ ያለባትን ከፍተኛ ድክመት ያሳያል። ሆኖም ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓለም አቀፍ ጨዋታዎች ያስመዘገበችው ዝቅተኛ የጎል አማካይ (በጨዋታ 0 ነጥብ 8 ጎል)፣ በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ ስር የሚገኘው ስብስብ በአጥቂ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄና ስራ እንደሚጠይቀው መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የመጀመሪያው ጨዋታ በሞሮኮ መደረጉ ለኢትዮጵያ እንደ ገለልተኛ ሜዳ የሚቆጠር ሲሆን፣ የመልሱ ጨዋታ በድሬዳዋ ስታዲየም መደረጉ ቡድኑን በከፍተኛ ስነ-ልቦና እንዲገፋ ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከዓመታት ስደት በኋላ በገዛ ሜዳው የመጫወት ዕድል ማግኘቱ፣ ከስፖርታዊ ድል ባለፈ ትልቅ ስነ-ልቦናዊና ሀገራዊ ፋይዳ አለው። በሌላም በኩል ሳኦ ቶሜን የመሰሉ ከባህር ጠለል በላይ ዝቅ ባለ ስፍራ የሚገኙ ሀገራት፣ በኢትዮጵያ ያለውን የከፍታና የአየር ጸባይ ተቋቁሞ መጫወት ፈታኝ ይሆንባቸዋል። ይህም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተፈጥሯዊ የሜዳ ላይ ብልጫን ይሰጣል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳው ወቅት ያለው የማሸነፍ ዕድል ከሜዳ ውጭ ካለው ጨዋታ በ65 በመቶ ብልጫ አለው። ይህ በሜዳ የመጫወት ዕድል፣ ለተጫዋቾች የሚሰጠው ስነ-ልቦናዊ መረጋጋትና ከጉዞ ድካም ነፃ መሆን፣ ለ2027ቱ የአፍሪካ ዋንጫ የሚደረገውን ጉዞ በስኬት ለመጀመር ወሳኝ ግብዓት ነው። በድሬዳዋ የሚደረገው የመልስ ጨዋታ፣ ዋሊያዎቹ ወደ ዋናው የምድብ ድልድል (48 ሀገራት ወደሚሳተፉበት) ለመሸጋገር ያላቸውን የላቀ ግምት ወደ እውነታ የሚቀይሩበት መድረክ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ የሚመራው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለዚህ ውድድር ትልቅ ተስፋ ሰንቆ ነው ወደ ውድድር ያቀናው። አሰልጣኙ ልምድ ያላቸውንና በሀገር ውስጥ ሊግ ብቃታቸውን ያሳዩ 23 ተጫዋቾችን ያካተተ ስብስብ የያዙ ሲሆን፣ ቡድኑ ካለፉት ሁለት የአፍሪካ ዋንጫዎች መቅረቱን ተከትሎ አሁን ዳግም ወደ አህጉራዊ መድረክ ለመመለስ ከፍተኛ መነሳሳት ላይ ነው። ከዚህ ቀደም ዋሊያዎቹ በ2018 የዓለም ዋንጫ ቅድመ ማጣሪያ ላይ ሳኦ ቶሜን በድምር ውጤት 3 ለ 1 አሸንፈው ማለፋቸው የሚታወስ ሲሆን፣ አሁንም ያንን ድል በመድገም ወደ ዋናው የምድብ ድልድል ለመቀላቀል ሰፊ ዕድል አላቸው ተብሎ ይታመናል። ይህ ጉዞ ዋሊያዎቹ ለአህጉራዊ ክብር ያላቸውን ናፍቆት የሚወጡበት የመጀመሪያው ወሳኝ ምዕራፍ ነው።

እንደ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን እና የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መረጃዎች መሠረት፣ ኢትዮጵያ በዚህ ደረጃ ማለፍ ካቃታት ወደ ዋናው የምድብ ድልድል (48 ሀገራት ወደሚሳተፉበት) መግባት አትችልም። የ2027 የአፍሪካ ዋንጫ (AFCON) የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች፣ በአህጉሪቱ ዝቅተኛ የፊፋ ደረጃ ያላቸው ስምንት ብሔራዊ ቡድኖች ወደ ዋናው የምድብ ድልድል ለመግባት የሚያደርጉት የ'ሞት ሽረት' ፍልሚያ ነው። እነዚህ ጨዋታዎች በሜዳና ከሜዳ ውጭ በሚደረጉ የደርሶ መልስ ውጤቶች የሚወሰኑ ሲሆን፣ አራት አሸናፊ ቡድኖች ብቻ ናቸው ቀሪዎቹን 44 ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ሀገራት ተቀላቅለው በ12 ምድቦች ውስጥ የሚደለደሉት።

ከ2012 በፊት የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያዎች ሁሉንም ሀገራት በቀጥታ በምድብ በመከፋፈል ይካሄዱ ነበር። ነገር ግን የተሳታፊ ሀገራት ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱና የጨዋታዎችን ጥራት ለመጠበቅ ሲባል፣ በፊፋ ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሀገራት እርስ በእርስ ተጫውተው እንዲያልፉ የሚያደርግ የቅድመ ማጣሪያ ስርዓት በካፍ ተዘረጋ። በተለይ እ.ኤ.አ ከ2019 የግብፅ የአፍሪካ ዋንጫ ጀምሮ የተሳታፊ ሀገራት ቁጥር ከ16 ወደ 24 ከፍ ማለቱን ተከትሎ፣ የማጣሪያው ሂደት ይበልጥ ስልታዊ እንዲሆን ተደርጎ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን 8 ሀገራት በማጣመር በቅድመ ማጣሪያው እንዲሳተፉና አሸናፊዎቹ ሀገራትም ወደ ዋናው የምድብ ድልድል እንዲቀላቀሉ ይደረጋል፡፡

ኢትዮጵያና ሳኦ ቶሜ እና ፕሪንሲፔ ከሚያደርጉት ውድድር በተጨማሪ ኤርትራ ከላይቤሪያ፣ ደቡብ ሱዳን ከሞሪሽየስ እንደዚሁም ቻድ ከሞሪታኒያ የቅድመ ማጣሪ ውድድሮችን የሚያከናውኑ ሀገራት ናቸው፡፡ አሸናፊዎቹ ቡድኖች በቀጥታ ወደ 48ቱ ሀገራት የምድብ ድልድል ውስጥ በመግባት፣ ቢያንስ ስድስት ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን የማድረግና ከታላላቅ የአፍሪካ ኮከቦች ጋር የመጋጠም ዕድል ያገኛሉ፡፡ በሰኔ ወር 2018 ዓ.ም ከሚጀመረው ዋናው የምድብ ማጣሪያ ይቀላቀላሉ።